# ሥርዓተ ጾታ



## መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የተደረጉ ጥናቶች በእጅጉ ውስን ናቸው። ነገር ግን ብዙ አስተዋይ ግለሰቦች ኢትዮጵያውያን ሴቶች በህይወት ዘመናቸው ምን አይነት አስቸጋሪ ኑሮ እንደሚኖሩ አስተያየቶቻቸውን አቅርበዋል።

ኑሮን አስቸጋሪ ከሚያደርጉባቸው አድካሚ ሥራዎች መካከል በየዕለቱ ረጅም መንገድ እየተጓዙ እንጨትና ውሃ ማመላለስ፣በእጅ መፍጨት፣ የቤት ውስጥ ሥራ ማከናወን፣ ልጆች መንከባከብ ይገኙበታል ከዚህም በተጨማሪ በተለምዶ ከሚደርስባቸው ልዩ ልዩ ተፅዕኖዎች በተጨማሪ ራሳቸውን በማጠናከር ረገድ በትምህርትና በሥራ ቅጥር ላይ ከወንዶች ያነሰ ዕድል ነበራቸው።

በኢትዮጵያ ከሰማኒያ አምስት በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ሥራ በሚተዳደሩ የአርሶ አደር ቤተሰቦች ውስጥ በገጠራማ አካባቢ ይኖራሉ። የገጠር ሴቶች ደግሞ ሰፊ የሰው ጉልበት በሚጠይቀውና ሕጻናትን ጨምሮ ሁሉም ሰው አድካሚ የጉልበት ሥራ ከሚሠራበት የገጠሩ የግብርና ኢኮኖሚ ጋር የተቆራኙ ናቸው። ሥር በሰደደው የቆየ ባሕላዊ እምነት የተነሳ የመሬት ስሪት ማሻሻያውም የሴቶችን የተቀጢላነት ደረጃ አላሻሻለውም። የሴቶች በኢኮኖሚ ሁኔታዎች መለወጥ ምናልባት የኑሮ ደረጃቸውን ያሻሽል ይሆናል። እውነተኛውን ለውጥ ለማምጣት ግን በሴቶች ላይ ያለንን

አመለካከት ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገርን ይጠይቃል፡፡

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሴቶች በግብርናው ዘርፍ የጎላ ድርሻ ቢኖራቸውም በሌሎች ታዳጊ አገሮች እንደሚኖሩት ሴቶች ሁሉ አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ሀብቶች ማለትም መሬት፣ እንስሳት፣ የእርሻ መሳሪያ ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ ዕውቀትና መረጃ የማግኘትና የመቆጣጠር ዕድላቸው አናሳ ነው ወይም ጨርሶ አይኖርም፡፡ ይህም በመሆኑ በግብርና ውጤቶች ምርትና ገበያ ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽዖና ሚና ያሳንሳል፡፡

ዓለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲ ጥናት ኢኒስቲትዩት (International Food Policy Research Institute, IFPRI) በ271 የዓለም ባንክ ፕሮጀክቶች ላይ በቅርቡ ባካሄደው ጥናት ፕሮጀክቶች የወንዱንም የሴቱንም ፍላጎቶች አካተው የሚሰሩ ከሆነ የውጤቶቻቸው ዘላቂነት በ16% እንደሚጨምር ለማወቅ ተችሏል ( Quismbing and Pondolfelli)፡፡ የግብርና ምርታማነትና የገበያ ማሻሻያዎችን ለማምጣት ተፈላጊ በሆኑ መረጃዎች ትምህርትና ሙያ ሴቶችን ለማብቃት የሚያስችሉ እርምጃዎች ሆን ተብለው ካልተወሰዱ በስተቀር ዘላቂ የግብርና ዕድገት ማግኘት ተጨባጭ ሊሆን አይችልም፡፡

ይህ ሰነድ የምርታማነትና ግብይት ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) ሥርዓተ ፆታን እንደ ተቀዳሚ ተግባር በመውሰድ የሴቶችን የሀብት ፣ የዘመናዊ አሰራርና የዕውቀት ተደራሽነትን ለማሳደግ ብሎም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸውን ለማሻሻል የተደረጉ ተሞክሮዎችን ያቀርባል፡፡ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ስልቶችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና ውጤቶችን ለማሳየት የተመረጡ ጉዳዮችን ጭምር አቅርቧል፡፡

ግኝቶቹ መሠረት ያደረጉት በምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) የስርዓተ ፆታ ቡድንና በአራት ክልሎች በሚገኙ በአሥር የሙከራ ጣቢያዎች የልማት ሠራተኞች ጥናት ላይ ነው፡፡

## በቅድሚያ የሥርዓተ ፆታ ትንተና

የሥርዓተ ጾታ ፅንሰ ሀሳብን ጠንቅቆ መረዳት የጾታ እኩልነትን ለመደገፍ የሚረዱ አጋጣሚዎችን ለመለየት በገበያ መር የግብርና ልማት ማበረታቻዎች ውስጥ የፆታ ተሳታፊነትን ለመደገፍ የሚረዱ አጋጣሚዎችን መለየትና ለፕሮጀክት ትግበራና ዘላቂነት ቁልፍ መሆናቸውን የምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) ይገነዘባል፡፡

በዚህም መሠረት የምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት የፆታ ትንተና ለገበያ የሚመረቱ ምርቶች ቅደም ተከተል የህብረተሰቡን ማህበራዊ ሀብት ገፅታዎችን፣ መህበራዊ ትስስሩን የአዳዲስ አሰራሮችን ተደራሽነትና አገልግሎቶችን መገንዘብ መቻል እንደ መጀመሪያ እርምጃ ወስዷል፡፡ የሥርዓተ ፆታ ትንተና ሦስት የተለዩ ዓላማዎች አሉት፡፡

- በግብርና ምርትና ገበያ እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የወንዶችና የሴቶችን የተለያዩ ሚናዎች የበለጠ ለመረዳትና ከጥቅሙም የሚያገኙትን ድርሻ ማወቅ፣
- ለወንዶችና ለሴቶች በገበያ መር የግብርና ልማት ማበረታቻዎችና ቴክኖሎጂ ስርፀት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን መለየት፣
- ጋሬጣዎቹን ለማስወገድ በፕሮጀክቱ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች መለየት፣

ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች የሴቶች ኃላፊነት በሆኑት በእንስሳት እርባታና በዋና ዋና ሰብሎች ምርት ዙሪያ የእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ሴቶች የጎላ ሚና እንዳላቸው በማስረጃ አስደግፈው አቅርበዋል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረት በምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ሥራዎች ውስጥ ሥርዓተ ጾታን ለማቀናጀት ውስጥ ገብቶ ማገዝ እንደ መነሻነት ለመሆን ችሏል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ገብቶ የማገዝ እንቅስቃሴዎች መሃል ለሥርዓተ ጾታ ግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፖችን በወረዳ ደረጃ ማዘጋጀት፣ በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጁ የድርጊት መርሃ ግብሮች ሥርዓተ ጾታን ያካተቱ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ሥርዓተ ጾታ ነክ ጥናቶችን



ማካሄድና ለፕሮጀክቱ ቁጥጥር የሚሆኑ የሥርዓተ ጾታ አመላካቾችን መለየት ይገኙበታል፡፡

### በሰብል ምርትና በእንስሳት እርባታ ውስጥ ፆታዊ የሥራ ክፍፍል

የሥርዓተ ጾታ ትንተና ለተስማሚ ሰብሎች፣ ለእንስሳት እርባታ ወይም ለወቅታዊ ሰብሎች ልዩነት መኖሩን እንደሚያመለክተው ምንም እንኳን የሥራ ክፍፍሉ በየሰብሉ ዓይነት ወይም እንደየአካባቢው የተለያዩ ቢሆንም አንድ ጠቅለል ያለ በእንስሳት እርባታና በሰብል ምርት ውስጥ ያለውን የተለየ የወንድና የሴት ሥራ ክፍፍል ማስቀመጥ ይቻላል (ለምለም አረጉ 2010)፡፡

### የሰብል ምርት (Arable crops)

ወንዶች በተለይ ከበድ ያለ ጉልበት ለሚጠይቅ ለምሳሌ በሰብል ምርት ውስጥ መሬትን ማዘጋጀትና በበሬ ማረስ የመሳሰሉትን የመስራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዘር መረጣ ወቅት ለመረጃ ያላቸውን ቀረቤታ በመመርኮዝ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ዘር እና ማዳበሪያ መዝራትም የወንዶች ሥራ ነው፡፡ በተለምዶ እህል መውቃትም ሆነ ማዳበሪያ መጨመር ወይም ማበራየት የወንዶች ኃላፊነት ነው፡፡

ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ ጥንቃቄና ትኩረት በሚጠይቁ ተግባራት ላይ የሚሰማሩ ሲሆን፣ ለምሳሌ በችግኝ ጣቢያዎች ችግኝ በማፍላት፣ አዛውሮ በማሳ ላይ መትከልና ማረም የመሳሰሉ ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከቤተሰብ ኃላፊነት ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ለምሳሌ ምርትን በጎተራ እንደማስቀመጥ፣ ለተፈላጊ ጉዳዮች እንዲውል አድርጎ በማዘጋጀት ወይም እሴት መጨመር የመሳሰሉት ሥራዎች በተለይ የሴቶች ድርሻ ናቸው፡፡

## እንስሳት እርባታ (Livestock)

ወንዶች ከፍ ያለ የገበያ ዋጋ በሚያስገኙ እንስሳት እርባታ ሥራ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን በተለይ እንደ ከብት፣ ፍየል፣ በግ፣ ግመል እርባታና ንብ ማነብ ውስጥ አብዛኛውን ሥራ ይሠራሉ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ከቤተሰባቸው ውጪ ከሆኑ አካላት ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን ለምሳሌ መረጃ የማግኘትን፣ ማዳቀል፣ ማርባት፣ የከብት ጤና አጠባበቅ በተለይ ዘመናዊ የከብት ሕክምና አገልግሎት የማግኘት ጉዳዮችን ማከናወን የወንዶች ኃላፊነት ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ከፍተኛ ጉልበት በሚጠይቁ እንደ ከብት እርድ ማከናወን ወይም በረት መሥራት የመሳሰሉት የወንዶች ድርሻ ናቸው፡፡

ሴቶች በእንስሳት እርባታ ውስጥ በተለይ በቤት አካባቢ በሚደረጉ በእንስሳት ጤና አጠባበቅና ደህንነት ላይ ያተኮሩ ለምሳሌ እበት መዛቅና የከብቶች ንፅህናን መጠበቅ በመሳሰሉ ሥራዎች ላይ ይሰማራሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ከቤተሰብ ኃላፊነት ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የእንስሳ ተዋፅዖን በማዘጋጀት፣ እንዳይበላሽ አድርጎ የማስቀመጥ፣ ጥቅም በሚውል መልኩ እሴት ጨምሮ ሳይበላሽ የማቆየት ሥራዎች የሴቶች ድርሻ ናቸው፡፡ የከብቶችን መኖ የማቅረብም ሆነ ውሀ የማጠጣት ሥራ አብዛኛውን ጊዜ በጋራ የሚሰራ ሌሎች የቤተሰብ አባላትም ሊሳተፉ የሚችሉበት ጉዳይ ነዉ፡፡

## ቋሚ ሰብሎች (Perennial Crops)

የቡና ተክሎችንና የፍራፍሬ ዛፎችን በማልማት ረገድ በእጅ የሚከናወኑ የጉልበት ሥራዎች፣ ለምሳሌ የመሬት ምንጣሮ፣ ቁፋሮ፣ የችግኝ መደብ ዝግጅት፣ አረም ማረም፣ መጎንደል የመሳሰሉት ሁሉ በወንዶች ይሰራሉ፡፡ እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ሚስቶች አብዛኛውን ጊዜ በአፈር ለምነት አጠባበቅ ሥራ፣ ምርት በመሰብሰብ ወይም በለቀማ፣ በአፈር ጥበቃና አያያዝ ላይ ይሰማራሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሴቶች ተሳትፎ ከፍ የሚለው የቋሚ ሰብሎች ተከላ የተከናውነው ከመኖሪያ አካባቢ የማይርቅ ከሆነ ነው፡፡

## የሰብልና የእንስሳት እርባታ ግብይትና ጥቅም መጋራት ረገድ የሥርዓተ ፆታ ሚና

ከምርት የሚገኘውን ጥቅም በመጋራት ላይ በሴቶችና በወንዶች መካከል የሚታይ ልዩነት አለ፡፡ ይህም በአመዛኙ በሚያበረክቱት የጉልበት ሥራ አስተዋፅዖ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የሚመረተው ምርት ለቤተሰብ ፍጆታ መዋል አለመዋሉን፣ በማህበረሰቡ ልማድ ሴቶችና ወንዶች የሚያከናወኗቸው ሥራዎች የሚሰጣቸው ግምት ወይም ሥፍራ እንዲሁም የየቤተሰቡ የሀብት ደረጃ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ምክንያት ጭምር የሚወሰን ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ በሥራ ጫናውና ከምርቱ በሚገኘው ጥቅም መጋራት መካከል ሚዛናዊነት ይጎላል፡፡ በአብዛኛው ከሰብል ምርቶችና ከከብት እርባታ የሚገኘውን ገቢ ወንዶች ወደመቆጣጠሩ ያዘነብላሉ፡፡ ምክንያቱም የእርሻ ሰብሎች አትክልቶችና የዛፍ ተክሎች ልማት ላይና በመጠኑ የትላልቅ እንሰሳት እርባታ ላይ ከሴት ጋር በጋራ ቢሰራም ከፍተኛውን የስራ ድርሻ የሚወስደው ወንዱ በመሆኑ ነው፡፡

እንደየወረዳው የሚለያይ ቢሆንም በአንዳንድ የማምረት ተግባራት፣ ለምሳሌ ከቅባት እህሎች፣ ከፍራፍሬ ዛፎች፣ ከቅቤ ከከብትና ከዶሮ እርባታ የሚገኙ ጥቅማጥቅሞችና የሥራውን ጫና ወንድና ሴት እኩል የሚካፈሉበት ሁኔታም አለ፡፡ በተጻራሪ ደግሞ በጣም አነስተኛ ይሁን እንጂ ሴቶች ከወንዶች ይበልጥ የሥራ ጫናውንም ሆነ የሚገኘዉን ጥቅም የሚቆጣጠሩበት የምርት ዓይነት አለ፡፡ ለአብነት በፎገራ የበርበሬ ምርት እንዲሁም በብዙ ሥፍራዎች የዶሮ እርባታ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ በጋራ ድካም ከተገኘው ገቢ ውስጥ ሴቶች የሚቆጣጠሩት ጥቂቱን ብቻ ነው ፡፡ በአላማጣ የፍራፍሬ ዛፎችና የዶሮ እርባታ በአጽቢ ወምበርታ፣ በፎገራ፣ በአድአ ሊበን፣ በዳሌ እና በአላባ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

## በግብርና አገልግሎቶች ተደራሽነት ውስጥ ፆታን መሠረት ያደረጉ ልዩነቶች

ምንም እንኳን ሴቶች ለግብርናው ምርታማነት በግብርናው ሥራ ከ40% እስከ 60% የሚደርስ አስተዋፅኦ ቢያደርጉም (ዓለም ባንክ 2008) በተለያዩ ደረጃዎች የሀብትና የአቅም ግንባታ ዕድሎች ተደራሽነት ያለመመጣጠን ችግር ይደርስባቸዋል፡፡ ስለዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ ምንም ዓይነት መደበኛ የሆነ ግንዛቤ ስለማይኖራቸውና ሙያቸውን ለማሻሻል ብዙም ዕድል ስለማያገኙ ባሎቻቸው ወይም ሌሎች ሰዎች በሚሰጡዋቸው መረጃ ላይ ወይም ባላቸው ግንኙነቶች የስሚ ስሚ በሚያገኙት መረጃ ላይ ለመመርኮዝ ይገደዳሉ፡፡

የወንዶችና የሴቶች የማህበራዊ ግንኙነትና የመረጃ ምንጭ ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው ሴቶች ለመረጃ፣ ቴክኖሎጂ፣ ለትምህርት ዕድልና ክህሎት ውሱን ተደራሽነት እንዳላቸው በግልፅ ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ በሴቶች እውቀትና ሙያ ማሻሻያ ሆነ የግብርና ምርቶችን ለማምረትና ለገበያ የማቅረብ ውሳኔ ላይ የሚንፀባረቅ በመሆኑ በግብርና ልማት ማስፋፊያ ስራ ላይ የከፋ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

አዳዲስ ዘመናዊ አሰራሮችን ወይም ቴክኖሎጂን የመቀበል ደረጃ ደሃ በሆኑ የአርሶ አደር ቤተሰቦች ሆነ በሴት በሚመሩ ቤተሰቦች ጭምር ሊደናቀፍ የቻለው አቅም በማጣት የብድር ቁጠባ ተቋማት



ውስንነት ጋር ተደምሮ የግንዛቤ ደረጃውም ዝቅተኛነት ጭምር በምክንያትነት ሊነሳ ይችላል፡፡

ሴቶች የግብርና ቴክኖሎጂን የመቀበልና ያለመቀበል ውሳኔ ውስጥ የሚሳተፉት በአብዛኛው በእማወራ በሚመራ ቤተሰብ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ወንዶች ዘሞዶቻቸውን በማማከር እንደሚወስኑም ይታወቃል፡፡

የሴቶችን የዕውቀትና የመረጃ ተደራሽነት ለማሳደግ፣ ቴክኒካዊም በሆኑትና ቴክኒካዊ ያልሆኑ ጉዳዮች ጭምር አቅማቸውን ለማጎልበትና በተመረጡ የእሴት ሰንሰለቶች ውስጥ ተሳትፎአቸውን ለማጎልበት የምርታማነትና ገበያ ስኬት ፕሮጀክት የሥርዓተ ፆታ ትንታኔ ላይ በመመርኮዝ ሴቶችን በፕሮጀክቱ ተግባራት ውስጥ ለማሳተፍ ስልት ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ግማሾቹ ስልቶች ገበያ ተኮር ምርቶች ላይ ያተኮሩ ሲሆን ግማሾቹ ደግሞ ሌሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ፡፡ የሚከተሉት የዚህ ፅሑፍ ምዕራፎች ፕሮጀክቱ የተጠቀመባቸውን ስልቶች ያብራራሉ፡፡

ከሥርዓተ ጾታ ትንተና የተወሰዱ ግኝቶች ሥርዓተ ጾታ ከገበያ ተኮር ምርቶች አኳያ

## ከገበያ ተኮር ምርቶች በተጨማሪ ያሉ ስልቶች

የሚያሳየውን የመረጃ ጥንቅር በማዘጋጀት እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ በገበያ ተኮር የግብርና ምርቶች እንቅስቃሴ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ማነቆ ሆነው የተገኙትንና የታወቁትን እንቅፋቶች ለማስወገድ የሚረዱ አማራጮች ዝርዝር በሀሳብ ማጠናቀሪያ ፅሁፎች እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የግብርናና ገጠር ልማት ሠራተኞች የግንዛቤ ደረጃና የሙያ ብቃት ሥርዓተ ፆታን በተያዘው የልማት ተግባር ውስጥ እንዲያካትቱ ማድረግ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ተከታታይ ወርክሾፖች ተዘጋጅተው ለማስተማሪያ በተመረጡ ወረዳዎች የስርዓተ ጾታ ጉዳዮች በድርጊት መርሃ ግብር ውስጥ እንዲያካትቱ ገለጻዎች ተደርገዋል፡፡ የልማት ሠራተኞች ሥርዓተ ፆታን በተፈለገው መጠን ከሥራቸው ጋር አካተው ለመስራት የሚያስችላቸው በቂ ሙያ እንደሌላቸው በመታወቁ በዚህ ረገድ ያለባቸውን ችግር ለመቅረፍና አቅማቸውን ለመገንባት ሥልጠናዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል፡፡ ትኩረቱም ለዚህ ጉዳይ የሚጠቀሙበት ተግባራዊ ክህሎትና የቁጥጥር ዘዴዎች ላይ ነበር፡፡

### ስለ ገበያ ተኮር የግብርና ምርት፣ አገልግሎትና ግብአት ዕውቀትና ሙያ እንዲያገኙ የሴቶችን ተደራሽነት ማሳደግ

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሴቶች ለመረጃ ያላቸው ተደራሽነት የተገደበ ነው፡፡ ስለዚህ ሴቶች ለመረጃ፣ ለዕውቀትና ምርት የማሳደግ ሂደት ልዩ ክህሎትና ሙያ የማዳበር ተደራሽነታቸው እንዲጨምር አማራጮችን የሚያቀርቡ የተለያዩ ስልቶችን ፕሮጀክቱ ነድፏል፡፡ ምክንያቱም ፕሮጀክቱ ለምርታማነት መጨመርና ውጤታማ ገበያ የሚገኝበትን ትምህርትና ሙያ አስፈላጊነት ማሳወቅ ዋነኛ ተግባሩ መሆኑን ያምናል፡፡

በዕውቀት መጋራትና አቅም ግንባታ ተግባራት ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የምርታማነትና ገበያ ስኬት ፕሮጀክት የተጠቀመው መሠረታዊ ስልት፤ ሥልጠና፣ የመስክ ጉብኝትና ሌሎች የእሴት ሰንሰለት ማበልፀጊያ የውስጥ ድጋፎች ይገኙበታል፡፡ የዕውቀት መጋራትና አቅም ግንባታ ተግባራት ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ምርታማነትና የገበያ ስኬት ፕሮጀክት የተጠቀመው ዓይነተኛ ስልት የሴቶች ተሳትፎ 50% መሆኑን እንደግብ በማስቀመጥ ነው፡፡

በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት (1998 - 2002 እ.ኤ.አ) 36% የሚሆኑ ገበሬዎች በእማወራ ከሚመሩ ቤተሰቦችና በአባወራ ከሚመሩ ቤተሰቦች በአቅም ግንባታ ተግባር ላይ በፕሮጀክቱ ትግበራ አካባቢዎች ለማግኘት ተችሏል፡፡ሴቶችንዓላማበማድረግማልማት ማለት በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ተሳትፎአቸውን እንዲያሳድጉ ማብቃት ማለት ነው፡፡

### በስልጠና ላይ የቦታ መረጣና የሠዓት አከባበር አስፈላጊነት

ሴቶች የግብርናው ዘርፍ የጉልበት ምንጭና የማህበራዊ ነክ ጉዳዮች ተሳትፎ ዋነኛ ተዋናዮች ብቻ አይደሉም፡፡ ሌሎች ቤተሰባዊ የሆኑ ከባድ ኃላፊነቶች እንደ ሕፃናት ማሳደግ፣ ምግብ ማብሰል፣ ውሃ መቅዳት፣ ማገዶ መልቀምና ንፅሕና መጠበቅ የመሳሰሉ ተግባሮችም ያከናውናሉ፡፡ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው በክረምትም ይሁን በበጋ ሴቶች በቀን ከ10-12 ሰዓት እንደሚሰሩ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ስልጠና ለማዘጋጀት የሴቶችን የየዕለት የስራ ሰዓት ማወቅና አመቺ ጊዜና ቦታ መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ ማንኛውም ተለምዶአዊ የኤክስቴንሽን አሰራር ፕሮጀክቱ ስልጠና ሊሰጥ የመረጣቸው ቦታዎች ለመንደራቸው ቅርብ የሆኑ አካባቢዎች ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ በዳሌ፣ በጎማ፣ በአዳ፣ በአፅቢ፣ በአላማጣ፣ በፎገራና በቡሬ የተደረገው ይኸው ነው፡፡

ይህ ስልት ብዙ ሴቶች ሳይቸገሩ በስልጠናው እንዲሳተፉ አድርጓቸዋል፡፡ አብዛኛው ስልጠና በንድፈ ሀሳብ ወይም በገለፃ ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን በተግባራዊ ሰርቶ ማሳያ የታገዘ ድርጊታዊ ስለነበር በሰልጣኞቹ ከፍተኛ አድናቆትን አግኝቷል፡፡

### ጥንዶችን ማሰልጠን

አብዛኛውን ጊዜ መረጃ፣ ዕውቀትና ክህሎት ከባል ወደ ሚስት እንደሚተላለፍ ይታመናል፡፡ ይህ ደግሞ ሴቶች በተለይ ያገቡ ሴቶች ወደ ስልጠና ወይም ስብሰባ ወይም ወደ ተመሳሳይ መድረኮች እንዳይጋበዙ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህንን

‹‹የጥንዶች ስልጠና›› ባልና ሚስት አብሮ የሚሰለጥኑበት የስልጠና ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ሴቶች ስለግብርና ምርቶችና አመራረት እንዲሁም ግብይት አስፈላጊውን መረጃ፣ ሙያና ትምህርት የማግኘት ዕድላቸውን ያሰፋል፡፡ ጥንዶቹ በኋላም በመረዳዳት፣ በመደጋገፍና በመግባባት ስለሚሰሩ ከሥልጠና በኋላ ባል ለሚስቱ በሚያስተላልፈው መረጃ ላይ ብቻ ከመመርኮዝ ችግር ያድናል፡፡ ይህ ዘዴ ሴቶች የመወሰን ድርሻቸውን በማሻሻል የትኛውን የአሰራር ዘዴ መጠቀም እንዳለባቸው ወይም የትኛውን ለገበያ የሚሆን ሰብል ማምረት እንዳለባቸው በቤተሰባቸው ውስጥ በሚደረገው ውሳኔ እንዲካፈሉ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሴቶችን የፆታ ልዩነት ልማድ በማስቀረት የፆታ እኩልነት እንዲመጣ በር ይከፍታል፡፡ (N. Alemayehu, RDO and H.Gudeta RDA, Ada’a Liben PLW).

ችግር በመገንዘብ ፕሮጀክቱ የተሻለ ነው ያለውን ‹‹የጥንዶች ስልጠና›› ዘዴ አመንጭቷል፡፡

## የልምድ ልውውጥ

በገበሬዎች መሀል የሚካሄዱ የልምድ ልውውጥ ሂደቶችየአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን አሰራር ለማሳየት ውጤታማ የአመራረት ዘዴዎችንና አንዳንድ የምርት ዓይነቶች ለገበያ የሚውሉበትን መንገድ በማሳየት የሴቶችን ተነሳሽነት በማስፈን አዲስ አሰራሮችን እንዲያበለጽጉ ያደርጋቸዋል፡፡ የምርታማነትና ገበያ ስኬት ፕሮጀክት (IPMS) ልምድ እንደሚያሳየው ጥናታዊ ጉዞዎች፣ የመስክ ጉብኝት የመሳሰሉት ሴቶች እንዲነቃቁ ግንዛቤያቸው ዳብሮ አዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲመሩና እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡

## የሌሎች ግብአቶችና አገልግሎቶች ተደራሽነት

ታታሪና ሥራ ፈጣሪ ሴቶች አዳዲስ ቴኪኖሎጂዎችን እንዳይቀበሉ በዋናነት እንቅፋት የሆነው ጉዳይ የመነሻ ገንዘብ እጥረት ተደራሽነታቸው አናሳ መሆን ነው፡፡ ምንም እንኳን አዎንታዊ ተፅዕኖ ያላቸው ፖሊሲዎች በአነስተኛ ብድርና ቁጠባ የገንዘብ ተቋማት አማካኝነት ለሴቶች የብድር አገልግሎት ሊያቀርቡ በሚችሉበት መልክ የተዘረጉ ቢሆንም አብዛኞዎቹ ሴቶች የብድር አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም የብድር ተቋማቱ ያበደሩት ገንዘብ ለመመለስ ዋስትና እንዲሆናቸው አዋጪና አስተማማኝነት ያለው የፕሮጀክት ሰነድ የሚጠይቁ በመሆኑ ነው፡፡

ምርታማናነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና የሚመለከታቸው የግብርናና ገጠር ልማት ሠራተኞች በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችና ሴቶችን የብድር መጠየቂያ ማቅረቢያው ዝግጅት ላይ የቴክኒክ እገዛ በማድረግ ሴቶች ለብድሩ ተደራሽ እንዲሆኑና ወደ ሥራ እንዲሰማሩ አግዘዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብዙ ሴቶች ችሎታቸውን በመጠራጠር የተሰማሩበት ተግባር ውጤት ለገበያ ቀርቦ ትርፍ የማያመጣ ስለሚመስላቸው ብድር ከመውሰድ ይቆጠባሉ፡፡ ይህንን ጉዳይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በአካባቢው በሚገኙ የገንዘብ ተቋማት በሚተዳደረው የ‹‹ብድር ማሻሻያ ሥራ ማዕቀፍ›› በኩል ሴቶችን ለማግኘትና ማዕቀፉንም ወደ ተቋምነት ለመለወጥና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ጥረት አድርጓል፡፡ ለዚህ እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለው በዳሌ ወረዳ ለሚገኙ ሴቶች ለጫጩት ማስቀፍቀፍና ሽያጭ ስራ የተሰጠ ብድርና በመኤሶ እና በጎማ ደግሞ በግና ፍየል ለማድለብ የተሰጠው ብድር ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## የግብዓትና የምርት ግብይት ተደራሽነት

ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ግብዓትን በአግባቡ መጠቀም ሴቶች የሚሰሩዋቸው ስራዎች ምርታማነት እንዲያድግ፣ ተጨማሪ እሴት እንዲፈጠር፣ አዲስ ምርት ወይም ሴቶች የተለየ ጥራት ያለው ምርት እንዲያመርቱ ያደርጋቸዋል (Everts 1999)፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መሻሻል የበለጠ ትርፍ ወደማግኘት ወደ አስተማማኝ ደረጃና ራስን ወደመቻል ይመራል፡፡

ሴቶች በአጠቃላይ ግብዓትን በመግዛትና በመደራደር ሂደት ውስጥ ብዙ ችግሮች ያጋጥማቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ግብይት አቅራቢዎቹንና (የግልም ይሁኑ የሕብረት ሥራ ማህበራት) ሴቶችን እንዲሁም ወንዶች ገበሬዎችን በወረዳ ደረጃ በሚገኙ የሙከራ ጣቢያዎች አካባቢ ለማገናኘት ሞክሯል፡፡ በተጨማሪ አስፈላጊውን ስልጠናና ብድርም ሰጥቷል፡፡ በጎማ በበግ ማድለብ ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች መኖ ከሚያቀርቡ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ተደርጓል፡፡ በዳሌ ደግሞ በዶሮ እርባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ከገዢዎች ጋር እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

በቡሬ፣ በዳሌና በጎማ የሚገኙ የፍራፍሬ ዛፍ ችግኝ አምራቾች ደግሞ ከገበሬዎች ጋር እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡ በአድአና በአላማጣ የሚገኙ ወተት አምራቾች ደግሞ ከወተት የህብረት ሥራ ማህበራት ጋር እንዲገናኙ የመኢሶ ፍየል አድላቢዎች ደግሞ ከገበያ ጋር እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

## ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና ማስተዋወቅ

ቀድሞ እንደተለመደው አስፈላጊ የሆኑ የቤተሰብ ንብረቶች እንደ መሬት፣ የእርሻ በሬዎች፣ ከብቶችና የእርሻ መሳሪያዎች ለወንዶች የተሰጡ ናቸው፡፡ ሴቶች እንስሳትን ተጠቅመው መሬት ማረስ ያልተለመደ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት



### የወ/ሮ ካሱ ምርታማነትና ገበያ ስኬት ፕሮጀክት ያከናወናቸውን ተግባራት ተዘዋውራ መጎብኘት

የምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) አማካኝነት በፍራፍሬ ችግኝ ማፍላት ሂደት ችግኝን ቆርጦ በመከተብ የማዳቀልን ዘዴ ከአሥር ወንድ አርሶ አደሮች ጋር ስልጠና ለመውሰድ ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም የፍራፍሬ ፍልና የበርበሬ ችግኝ በሰርቶ ማሳያነት እንዳውለው ተሰጥቶኛል፡፡ እንዲሁም ደግሞ 10 ሆነን (ሦስት ሴቶችና ሰባት ወንዶች) የልምድ ልውውጥ ጉዞ ለ14 ቀናት በኢትዮጵያ ውስጥ ሲደረግ የመካፈል ዕድሉ ገጥሞኛል፡፡

የምርታማነትና ገበያ ሰኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልሎች ያከናወናቸው ተግባራት በመስክ ላይ ይገኛሉ፡፡ የመስክ ጉብኝቱ ጉዞ ለኔ ልክ እንደ ሕልም ነበር፡፡ እንደ አንድ ባሏ በሞት የተለያት ሴት ሆኜ ሳስበው እነዚህን ቦታዎች የመጎብኘት ዕድል ይገጥመኛል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ከቡሬ ወረዳ የወጣሁት አንድ ጊዜ ነው፡፡ እሱም ባህርዳር ለመሄድ ነበር፡፡ በአሁኑ ጉዞዬ ብዙ ልጠቀምባቸው የሚገቡኝ ነገሮች ተመልክቻለሁ፡፡ የዶሮ እርባታና፣ የጓሮ አትክልቶች ልማት ካየኋቸው ጠቃሚ ነገሮች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ እስከአሁን ግማሾቹን ምልከታዎቼን የከተማ ግብርና ቴክኒኮችን ጨምሮ በተግባር ተርጉሜያለሁ፡፡

የእርሻ በሬዎች ያሉዋቸው እማወራዎች እርሻቸውን ለማረስ ገንዘብ ከፍለው ወንድ መቅጠር ወይም በሬያቸውን በመስጠት መሬታቸውን በሚያርስላቸው ሰው ጉልበት መለወጥ ይኖርባቸዋል። ስለዚህም እንዲህ አይነቱን ልማዳዊ እንቅፋት የሚያስከትለውን ተፅእኖ ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና በማስፋፋት ማስወገድ ይቻላል።

## ምጣኔያዊ የአስተራረስ ዘዴ (Conservation Tillage)

በመተማና በቡሬ ወረዳዎች መሬት ከመዘራቱ በፊት ከሶስት እስከ አራት ጊዜ ጥማድ በሬ በመጠቀም ከታረሰ በሁዋላ በመጨረሻ ደግሞ የተዘራውን ዘር ለማልበስ እንደገና ይታረሳል። እርሻውም የቤተሰብ መሪ አባወራ የሚያርሰው ሲሆን፤ ዘር የመዝራቱን ተግባር ደግሞ ሌላ ሰው ያከናውናል። አብዛኛውን ጊዜ በእማወራ የሚመራ ቤተሰብ ቢኖረው አንድ በሬ ነው፣ አለበለዚያ ጭራሹንም የለውም። ይህ ደግሞ መሬታቸውን የማረስ አቅማቸውን ይገድበዋል። በግብርና ሥራ ውስጥ አረም የማረም ሥራ አብዛኛውን የሚከናወነው በሴቶችና በልጆች ነው። በመተማና በቡሬ የፕሮጀክት አጥቢያዎች ቁፋሮን የሚያስቀር የአስተራረስ ዘዴ (conservation tillage ) ፀረ-አረም መድሃኒት በመጠቀም ደጋግሞ ሳይታረስ የመዝራት ዘዴ አዲስ አሰራር በሙከራ ታይቷል። በቡሬ ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ከወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ሠራተኞች ጋር በመተባበር አዲሱን ቴክኖሎጂ ከማስተዋወቁም በላይ ስልጠናም ለጥንዶች አዘጋጅቷል። ከዚህም በተጨማሪ በመስክ በተግባር የተደገፈ ምልከታ በወንድም በሴትም ለሚመሩ ቤተሰቦች አሳይቷል።

> ከጥንዶች ስልጠና በኂላ አዲሱን አሠራር ወይም ቴክኖሎጂ ለመቀበል በጣም ቀላል ነበር። ምክንያቱም ውሳኔውን በጋራ መወሰን ስለቻልን ከስልጠናው በኂላ በጥሩ ሁኔታ መሳተፍ ጀምሬአለሁ። በተለይ መድሃኒቱን አደባልቆ የመርጨት ተግባር ላይና የሚዘራውን ዘር በማዘጋጀት በኩል ጥሩ ተሳታፊ ነኝ ።
>
> አበባየሁ አደም ከቡሬ ወረዳ

ምጣኔያዊየአስተራረስዘዴ(Conservation tillage) በሴቶችም በወንዶችም በኩል መሬት ለማዘጋጀትና አረም ለማጥፋት የሚያስችል ጊዜንና ጉልበትን የሚቆጥብ አዲስ ቴክኖሎጂ ሆኖ ቀርቧል። በርግጥም ደጋግሞ ማረስን የመከላከል ዘዴ ለሴቶች አዲስ ተስፋን ፈንጥቋል። ፀረ-አረም መድሃኒት (bio degradable pesticide) በመርጨት አረምን አጥፍቶ የሴቶችንና የቤተሰቡን አረም በማረም ይውል የነበረውን ጉልበት ማዳን ተችሏል።

ደጋግሞ ማረስን የመከላከል ዘዴ ስንጠቀም ዘር ከመዝራት በፊት የነበረውን አድካሚ የማረስና የመቆፈር ሥራ ትተን መድሃኒት በመርጨት ስንተካው እርሻ የሚታረሰው የተዘራውን ዘር በአፈር ለማልበስ ብቻ ይሆናል።

ይህ አዲስ የአስተራረስ መንገድ ለሴቶች በባህላዊው መንገድ ከ3 እስከ 4 ጊዜ በየሰብሉ ዑደት መቅጠር የነበረባቸውን የሰው ጉልበት ወደ አንድ ጊዜ ብቻ እንዲያሳንሱ ይረዳቸዋል። ይህ ደግሞ ራሱን በቻለ የሴቶችን ጊዜ የመቆጠብና ለሌላ አስፈላጊ ጉዳዮች የማዋል መልካም ዕድል ይፈጥራል።

## ሴቶችን በማሳረስ ሰፍኖ የቆየውን ልማድ መስበር

በኢትዮጵያ በበሬ ማረስ የወንዶች ሥራ መሆኑ ልማዳዊ ሆኖ ቆይቷል። ስለ ሥርዓተ ፆታ መሠረታዊ ጉዳዮች በወረዳ ደረጃ በሚገኙ 10 የሙከራ ጣቢያዎች በተደረገ ጥናት ሴቶች በሬ እርፍ ጨብጠው አያርሱም። ነገር ግን በእጅ መቆፈሪያ ተጠቅመው ይቆፍራሉ። ይህ

### አረጋሽ፣ እማወራ አርሶ አደር ከመተማ ወረዳ



በአዲሱ አሠራር መድሃኒት በመርጨት በሚሠራው ምጣኔያዊ የአስተራረስ ዘዴን ካየሁ በኂላ በአሠራሩ ለመጠቀም ፍላጎቱ ስላደረብኝ የመድሃኒት መርጫውንና መድሃኒቱን ለመግዛት ወሰንኩ። አሁን የራሴ መርጫ አለኝ፤ ራሴም እረጨዋለሁ። በአረም ማረም ስራ ላይ አባክነው የነበረውን ጉልበትና ገንዘብ ለማዳን አስችሎኛል። የበለጠ የጤፍ ምርት እንዳመርት ረድቶኛል። መድሃኒቱ ሸክማችንን አቅሎልናል ‹‹ገላገለን ››።

### ወይዘሮ አበባ የለውጥ ገበሬ



አበባ ከአባቷ ጋር በመሆን የእርሻ መሬት በማረስና ሰብል በማጨድ ተግባራት ላይ ትሳተፍ ነበር። በትምህርት ቤቷም ከወንድ እኩዮቿ እኩል የእግር ኳስ ፣ የእጅ ኳስና ሌሎች ስፖርቶችን ትጫወት ነበር። ከዚህ የተነሳ አስተማሪዎቿና ተማሪ ጓደኞችዋ በሁሉም ስራዋ በጣም ያደንቋት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ጓደኞቿና የሰፈር ገበሬዎች የባህላችን ውጤት አይደለችም ይሏታል።

በ2000 ዓ.ም በምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና በቡሬ ወረዳ በሴቶች ጉዳይ ቢሮ የተዘጋጀ የፆታ እኩልነትና በመወያየት የመግባባት ስልጠና በበሬ የማረስ ሰርቶ ማሳያ ስልጠና ላይ ተካፈለች። ከዚህ በኂላ አኗኗራቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ ከባለቤቷ ጋር ተወያየች። ከነበራቸው ሶስት አራተኛ ሄክታር መሬት ላይ በዓመት ግምቱ ከ4000.00 ብር የማይበልጥ 20 ኩንታል በቆሎና ስንዴ ያመርቱ ነበር። ከስልጠና በኂላ በ2001 ዓ.ም በኪራይ ሁለት ከሩብ ሄክታር የሚሆን መሬት ተከራዩ። ይህ ደግሞ በ2001 ዓ.ም 30 ኩንታል በቆሎ፤ 6 ኩንታ ስንዴና 12 ኩንታል በርበሬ ለማምረት አስቻላቸው። በ2002 ዓ.ም ደግሞ 35 ኩንታል በቆሎና 13 ኩንታል ስንዴና 10 ኩንታል በርበሬ ለማምረት ቻሉ።

ይህ ምርት ደግሞ በዓመት 24.000.00 ብር ገቢ ለማስገኘት ችሏል። ይህ ተጨማሪ ገቢ ሊገኝ

የቻለው በባልና ሚስቱ የተቀናጀ ጥረት ነው፡፡ እሷ በበሬ በማረስ ፣ ዘር በመዝራትና ወደ ገበያ በመሄድ ታግዘዋለች፡፡ እሱም በበኩሉ ልጆችን በመንከባከብ፣ የማገዶ እንጨት በማስቀመጥና ወጥ በመስራት እንዲሁም ደግሞ ልብስና የቤት ዕቃ በማጠብ የቤቱን ሥራ ያግዛታል፡፡

ልማድ ደግሞ በሴቶች ለሚመራ ቤተሰብ በተለይ ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጆች ወይም ወንድ ዘመድ ለሌላቸው ፈታኝ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ከዚህም በላይ በሴቶች በሚመራ ቤተሰብ ውስጥ ያሉት ሴቶች ያላቸው የከብት ብዛት በወንድ ከሚመራ ቤተሰብ ያነሰ ነው (ቶርክልሰን እና ጣሰው፣ 2008)፡፡ ስለዚህ በቂ የእርሻ መሬት ያላቸው በሴት የሚመሩ ቤተሰቦች አነስተኛ ወይም ምንም የእርሻ መሳሪያ የሚጎትቱ እንስሳት ስለሌላቸው ለገበያም ይሁን ለፍጆታ የሚሆን የግብርና ምርት ማምረት አይችሉም ማለት ነው፡፡

ይህንን መሠረታዊ ችግር ከግምት በማስገባት ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ከወረዳው የግብርናና ገጠር ልማትና የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመተባበር ይህንን ወግና ባህል በመስበር ሴቶች ማረስ እንደሚችሉ ለማሳየት ተሞክሮአል፡፡

## ስኬታማ ለሆኑ ሴቶች ዕውቅና መስጠት

የልማት ተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ፆታዊ ቁሳቁሶችን ማለትም የሥርዓተ ፆተ መረጃ ሰነድና የንብረት መረጃ ሰነድ የመሳሰሉት ለልማት አጋሮች ከማቅረብም በላይ የምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) በተለያዩ ዝግጅቶች ለስኬታማ ሴቶች ዕውቅና ሰጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ ሴት አርሶ አደሮች ምን ያህል አቅም እንዳላቸው የሰዎችን አመለካከት ለመለወጥ ይረዳል፡፡

### የበጎች ማድለብ ውድድር

በጎማ ወረዳ 120 አርሶ አደሮች ተጨማሪ የበግ መኖ እያስተዋወቁና የተቀነባበረውን መኖ ለመግዛት ብድር በመውሰድ የበግ ማድለብ ሥራ ጀመሩ፡፡ በዚህ መርሀ ግብር ውስጥ 50% የሚሆኑ ሴቶች እንዲታቀፉም ታስቧል፡፡ ይሁንና አርሶ አደሮቹን ለመምረጥ የተመደቡ የማህበረሰቡ መሪዎች መርሃ ግብርን ውጤታማ ለማድረግና ትርፍ አግኝቶ ብድሩንም መክፈል እንዲችል ለማድረግ በሴቶች አቅምና ችሎታ ላይ እምነት ስላልነበራቸው የተመረጡት ሴቶች 32% ብቻ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ በመርሃ ግብሩ ተግባር ላይ እንደተስተዋለው ግን አብዛኛው በማድለብ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ወንዶችን በውጤት በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ይህንን እውነታ ማህበረሰቡ እንዲያውቀው ለማድረግ የበግ ማድለብ ውድድር ለማድረግ ወሰነ፡፡

በምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና በወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት እንዲሁም በሴቶች ጉዳይ በተዘጋጀው ውድድር ከ120 አርሶ አደሮች አንደኛና ሁለተኛ በመሆን የተመረጡት ሴቶች ነበሩ፡፡ ለሚቀጥለው የማድለብ ሥራ እንዲሆናቸው አንድ ኩንታል መኖ በሽልማት ተስጥቷቸዋል፡፡ ውድድሩ ለማህበረሰቡ አባላትና መሪዎች ሴቶች የግብርና ምርቶችን የመምራትና ውጤታማ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የሚያስገነዝብ ዕድል ፈጥሮአል፡፡ በዚህም ምክንያት በሁለተኛውና በሦስተኛው የማድለብ መርሃ ግብር የተሳታፊ ሴቶች ብዛት ከ50% ሊያልፍ ችሏል፡፡

### የሴቶች የመስክ ጉብኝት ቀን በአድአ

በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮና በምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት አዘጋጅነት በሁሉም የገበሬ ማህበራት ውስጥ የሚገኙ ሴት አርሶ አደሮች በወተት ምርት፣ በአትክልትና በንብ ማነብ ምርትና ገበያ ላይ ተሰማርተው ውጤታማ ወይም ምርጥ አምራች የሆኑ ሴት አርሶ አደሮችን እንዲጎበኙ የመስክ የጉብኝት ቀን በአድአ የሙከራ ጣቢያ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ ይህ ዝግጅት ሴቶች ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በአግባቡ ከተጠቀሙ ምን ያህል ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ በወረዳው ለሚገኙ ሴት አርሶ አደሮች ለማሳየት አስችሎአል፡፡



**ሚስኩ - በግ መሸጥ በማህበረሰቡ ዕውቅናን አስገኘ**

ሚስኩ አባፋሪስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀች በጎማ ወረዳ የምትኖር የ42 ዓመት ሴት አርሶ አደር ናት፡፡ ገና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለች እንድታገባ ስለተደረገች አሁን የአምስት ልጆች እናት ናት፡፡ ሚስኩና በበግ ማድለብ ሙያ ላይ የተሰማሩት የቡድን አባላቷ ከምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና ከወረዳው የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በዱቤ አምስት አምስት በጎች ለያንዳንዳቸው ተሰጣቸው ፡፡ ሚስኩ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሁለት ዙር 12 በጎችን ለመሸጥ ችላለች፡፡ ሚስኩ የተጨማሪ መኖ ቴክኖሎጂን በጣም ትመርጣለች፡፡ ምክንያቱም ከባህላዊው ዘዴ ጋር ሲነፃፀር በአጭር ጊዜ ውስጥ በጎችን ለማድለብ ያስችላል፡፡

የበግ ማድለብ ሥራውን ከሌሎች የግብርና ሥራዎችና የቤት ውስጥ ጉዳዮች ጋር በማጣመር ትሰራለች፡፡ ውሳኔ ከባለቤቷ ጋር በጋራ ስለሚሰጡ ከሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ትቆጣጠራለች፡፡ “ከእንግዲህ ለቤት አስቤዛ ሆነ ለሌላ ወጪ የባለቤቴን እጅ አልጠብቅም፣” ብላለች ምስኩ፡፡ “ይህ ደግሞ ለኔ ትልቅ ለውጥ ነው”፡፡ ውጤታማነቷና ተጨማሪ ገቢዋ በማህበረሰቡ ዘንድ ታዋቂ አድርጓታል፡፡ በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮና በምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በተዘጋጀው የበጎች ማድለብ ውድድር ላይ ስላሳየችው ጥሩ አፈጻጸም ተሸላሚ

# የገበያ ምርት ተኮር ስልቶች (Commodity specific strategies)

በሁሉም የፕሮጀክቱ የመማሪያ ወረዳዎች በዋና ዋና ገበያ ተኮር ምርቶች ላይ የተዘጋጀው የስርዓተ ፆታና የሥራ ክፍፍል መረጃ የያዘ ጽሑፍ በእነዚህ ምርቶች አመራረት ሂደት የሴቶችና የወንዶችን ድርሻ ዝርዝር መረጃና ትንተና ያሳያል። በነዚህ የተለያዩ ምርቶች ሴቶች ኃላፊነት በሚወስዱባቸው ተግባራት፣ ባላቸው ውሳኔ የመወሰን አቅምና ገቢን የመቆጣጠር ወይም የሚገኘውን ጥቅም የመካፈል ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ምርት ነክ ስልቶችን ለመንደፍ ችሏል። ይህ ደግሞ ሴቶች በግብርና ምርቶችና ግብይት ውስጥ የበለጠ እንዲሳተፉ ለማድረግ ይረዳል።

## በተለምዶ የሴቶች ድርሻ የነበሩ የግብርና ዘርፎችን ማጠናከር

ምንም እንኳን በሰብል ምርትና በእንስሳት እርባታ ወንዶች ቁልፍ ሚና ቢኖራቸውም፣ በዚህም ምክንያት ከምርቶች ሽያጭ የተገኘውን ገቢ በበላይነት የሚቆጣጠሩት ወንዶች ቢሆኑም አንዳንዴ ከዚህ ወጣ ያለ ልምድ ይስተዋላል። ሴቶች በነዚህ ምርቶች አስተዳደርና አመራር ላይ ድርሻ የሚወስዱበትና ከሽያጭም ጥቅም የሚያገኙበት ሁኔታ አለ።

በምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት የማስተማሪያ አካባቢዎች በሙሉ የሥረዓተ ፆታ ትንተና ጥናት እንደሚያሳየው የዶሮ እርባታና የወተት ምርት የመሳሰሉት ዘርፎች ላይ ሴቶች ሥራውንም ጥቅሙንም በበላይነት ይመራሉ ወይም ሥራውን በበላይነት መርተው ጥቅሙን በጋራ ከባሎቻቸው ጋር ይካፈላሉ።

የግብርና ምርቶችን ለገበያ ማዘጋጀት ሥራን በሴቶች ዘንድ ለማሳደግ ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ከግብርናና ገጠር ልማት ጋር በመተባበር የዶሮ እርባታ ምርቶችና የወተት ምርት የገበያ አቅርቦት እንዲጨምር አዳዲስ ቴክኖሎጂን የማስተዋወቅና የገበያ ትስስር የመፍጠር ሥራ ሰርተዋል። ፕሮጀክቱ በሴቶች ላይ ትኩረት ከማድረጉም በላይ በእንቅስቃሴው ሂደት ልዩነት ያልተደረገባቸው መሆኑን በማረጋገጥ ሥራውን ያከናውናል።

## የዶሮ እርባታ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ

የዶሮ እርባታ ሰፊ መሬትና በዛ ያለ መነሻ ገንዘብ አይጠይቅም። የዶሮ እርባታ በራስ መተማመን ያጎለብታል። ምክንያቱም ከዶሮና ከእንቁላል የሚገኘው ገቢ ፈጣን የጥሬ ገንዘብ ማግኛ በመሆኑና በገቢውም ላይ የሚወስኑት ሴቶች በመሆናቸው የቤት ወጪያቸውን ይደጉምላቸዋል።

በምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በተደረገው ጥናት በዶሮ እርባታ ውስጥ አብዛኛው ስራ በሴቶች የሚሸፈን ነው። ጫጩት ማስፈልፈል፣ ንፅህና መጠበቅ፣ መመገብ፣ ውሃ ማጠጣት፣ ከጥቃት መጠበቅና እንደእንቁላል መሰብሰብ የመሳሰሉ ተግባራት በሴቶች የሚከናወኑ ናቸው። በቡሬና በአላባ ወንድና ሴት የሥራ ሚናውንና ገቢውን እኩል ከሚካፈሉበት በስተቀር በአብዛኛው ቦታ ከእንቁላልና ከዶሮ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ የሚቆጣጠሩት ሴቶች ናቸው። ምንም እንኳን በሁሉም የሙከራ ጣቢያ እንደታየው ከሚረቡት ዶሮች ግማሽ ያህሉ የሚሸጡ ቢሆንም የእርባታ ሥራው የሚካሄደው በአነስተኛ ደረጃ በባህላዊ ዘዴ ነው። አርቢዎቹ ምርጫቸው አነስተኛ ምርት የሚሰጡትን አገር በቀል የዶሮ ዝርያ ነው። ምክንያቱም ማርባቱ ብዙ ድካም ስላሌለበትና በቀላሉ መቆጣጠር ስለሚቻል ይመስላል። ስለሆነም ሴቶቹ የሚያገኙት ገቢም ጭምር አነስተኛ ነው።

ይህንን ሁኔታ ከግምት በማስገባት ምርታማነትና የገበያ ስኬት ፕሮጀክት የዶሮ እርባታን ምርታማነት ከፍ ለማድረግ ሽያጩንም ለማሳደግ የተለያዩ ይዘት ያላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ ጥረት አድርጓል። የአንድ ቀን እድሜ ያላትን ጫጩት ለሃያ ሳምንት የማሳደግ አዲሱ ዘዴ በዳሌ ወረዳ የከተማውንና የከተማ አቅራቢያ መንደሮችን አርሶ አደሮች እያደገ የሚሄደውን የዕንቁላል ጣይ ዶሮ ፍላጎት ማሟላት ባልተቻለ ቦታና አቅርቦቱ አነስተኛ በሆነበት ቦታ ማስተዋወቅ አንዱ መንገድ ነበር።

በምርታማነትና ገበያ ስኬት ፕሮጀክትና በወረዳው ግብርና ቢሮ 80 ሴቶች የተሳተፉበት አንድ የማሳዳጊያ ዕቅድ ተነደፈ። ለያንዳንዱ ሴት አንድ የገለባ ሙቀት መስጫ ሳጥን (Hay box brooder) ከውሃ ማጠጫ ጋር፣ 50 የአንድ ቀን ዕድሜ ያላቸው ጫጩቶችና ለሦስት ወር የሚሆን መኖ በዱቤ ተሰጠ። በወረዳ ደረጃ በሚገኙ የግብርና ቢሮና የምርታማነት ማሻሻያ ፕሮጀክት በመንደር ደረጃ ስልጠናና ያላቋረጠ የቴክኒክ ድጋፍ ተደረገላቸው። በወረዳ ደረጃ በሚገኙ የእንስሳት ሀኪሞች ምክር እየታገዙ ሴቶቹ ዶሮዎቻቸውን አስከተቡ።

> በማህበር የተደራጁ ሴቶች በጥሩ ሁኔታ በተዘጋጀ የስራ ዕቅድ እየተደገፉ የዶሮ እርባታ የእሴት ሰንሰለት አካል ሆነው ዘላቂ ለሆነ የግብርና ልማት የተዋጣለት የቁብ ዶሮችና የዕውቀት አቅራቢ መሆን ችለዋል፡፡

እነዚህ ዶሮዎች ለ173 ከተማ ቀመስ አርቢዎችና ለ400 የገጠር ቤተሰቦች ተሸጡ። በእያንዳንዱ ቤተሰብ ያለች ሴት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ብር 1071.78 ገቢ ለማግኘት ችላለች።

ሴቶችን ለእሴት ሰንሰለቱ ግብአት አቅራቢ አድርጎ ለይቶ ማወቅ፣ ቁብ ዶሮዎችንና ሴቶች ራሳቸው ክትባት መስጠታቸው የማይታሰብ ነገር ወይም የማይደረግ ነገር አለበለዚያ የተዘነጋ ጉዳይ ነበር።

ይህ ፕሮጀክት ከሌሎቹ በወረዳው ከሚገኙ የሥራ መስኮች ሁሉ በተለየ መልኩ ለሴቶች ትኩረት የሰጠ የመጀመሪያው ፕሮጀክት ነው። ምክንያቱም ብድር ማግኘት ስለሚችሉና ማህበሩም ሙሉ በሙሉ በራሳቸው የሚመራ በመሆኑ ነው። ይህ ደግሞ እነሱንም አነቃቅቷል። ከመስክ ሠራተኞችም ትኩረት እንዲያገኙ አድርጎአል።

### ራዲያ ቶምሲሳ፡- ከዶሮ እርባታ ጋር ወደፊት

ራዲያ ቶምሲሳ በዳሌ ወረዳ የአንድ ቀን እድሜ ያላቸውን ጫጩቶች ካሳደጉት ሴቶች አንዷ ናት፡፡ ከአንድ አመት በፊት ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በምትኖርበት አካባቢ ስልጠና ሲሰጥ እሷም አንዷ ተካፋይ ነበረች፡፡ ስልጠናው ከተሰጠ ከስምንት ወራት በኂላ 57 ቀን ዕድሜ ያላቸው ጫጩቶች ተሰጣት፡፡ ጫጩቶቹን ለመውሰድ የቅድሚያ ክፍያ ብር 150 ያስፈልጋት ነበር፡፡ ባለቤቷ ትልቁ ልጇና እሷ ሆነው አዋጥተው ጫጩቶቹን ወሰደች፡፡ ከ90 ቀናት በኂላ 49 ዶሮዎችን በ50 ብር ሂሳብ ሽጣ የ1300 ብር እዳዋን ከፍላ የ1150 ብር ንፁህ ትርፍ ባለቤት ሆነች፡፡ ከዚህ ውስጥ የቅድሚያ ክፍያ በማዋጣት ለረዳት ለባለቤቷና ለትልቅ ልጇ ሁለት ሁለት መቶ ብር ሰጥታ ቀሪውን ብር ለራሷ ወሰደች፡፡ ምክንያቱም የእርባታውን ሥራ ትሠራ የነበረው ብቻዋን ነበር፡፡ በሁለት መቶ ብር አንድ ፍየል ስትገዛ ልጇ ደግሞ አንድ ጥጃ ገዛ፡፡ እንድታረባ የተሰጣት ጫጩቶች ዱሮ እሷ በመንደሯ ከምታውቃቸው የአካባቢው ጫጩቶች በላይ በፍጥነት የሚያድጉ ነበሩ፡፡

**እንደ ዶሮ እርባታ የመሳሰሉ በልማድ በሴቶች የበላይነት የሚሰሩ ስራዎችን መደገፍ ከፍ ላለ ተጨማሪ የልማት ተሳትፎ እንደ መግቢያ በር ያገለግላል፡፡**



## የወተት ሀብት ልማትን ማሻሻል

በሁሉም የሙከራ ወረዳዎች አካባቢ የወተት ፍላጎት በአሁኑ ሰዓት እያደገና እየጨመረ ነው፡፡ ወተት በቀላሉ የሚሸጥ ሲሆን ከማምረትም ሆነ ከመሸጡ ሥራ ጋር በእጅጉ የተቆራኙት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ወተቱንም ሆነ ቂቤውን የሚሸጡት ሴቶች ሲሆኑ ገቢውንም የሚቆጣጠሩት ሴቶች ናቸው ይሁንና ማህበረሰቡ አገር በቀል ዝርያ ብቻ ስለሚያረባና የሚግጡትም ልቅ ሜዳ ላይ በመሆኑ የሚሰጡት ወተት አናሳ ነው፡፡ ምክንያቱም የተሻሻሉ ዝርያዎችን ወይም የተሻሻሉ ዝርያዎችንና ተጨማሪ የመኖ አቀራረብን ለማህበረሰቡ ማስተዋወቅ የወተት ምርቱን ማሳደግና የሴቶችን ገቢ የማሻሻል አቅም ይጨምራል፡፡

## በመኖና በድርቆሽ ዝግጅት ላይ ሴቶችን ማበረታታት

በገጠር አካባቢ በጓሮም ይሁን በግጦሽ ቦታ ድርቆሽን ማዘጋጀት በሴቶች ገቢ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አለው፡፡ ምክንያቱም በቤተሰብ ደረጃ መኖ የሚሰጠው ለሚታለቡ ላሞች ስለሆነ ብዙ ወተት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡

በሁሉም የምርታማነትና ግብይት ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) የመማሪያ ወረዳዎች ሴቶቹ ቅቤ ንጠው ያወጡና ይሸጣሉ፡፡ ገቢውንም ራሳቸው ይቆጣጠራሉ፡፡



### ራሶ ኡስማን በመኢሶ የመኖ አዘጋጅ አርሶ አደር

ራሶ ኡስማን በመኢሶ ወረዳ ድርቆሽ ለእንስሳት መኖነት ስታመርት ሦስት ዓመት ሆኗታል፡፡ ስለ አገር በቀል ዝርያ ከብቶችና ስለድርቆሽ ዝግጅት ባላት ልምድ ላይ ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት አብሮአቸው ከሰራቸው ሴቶች አንዱዋ ናት፡፡

ይሁንና የምታገኘው የወተት መጠን አናሳ በመሆኑ የተሻለ ምርት ወደሚሰጠው ቦረና ወደሚባለው ዝርያ ለመሸጋገር ወሰነች፡፡ በ 2001 ዓ.ም. በምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና በግብርና ቢሮ ድጋፍ ራሶ በአንድ ሄክታር መሬት ላይ ከማሽላ በጣምራ ለድርቆሽ የሚሆን መኖ አመረተች፡፡ የዚህ አዲስ አሰራር አላማ ከብቶቿን በጥሩ ሁኔታ መመገብ እንዲያስችላት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የወተት ምርቷ ከአንድ ሊትር በየቀኑ ወደ ሶስት ሊትር ሊያድግ ችሏል፡፡

ከብቶቿን ዓመቱን በሙሉ በበጋውም ወራት ለመቀለብ ችላለች፡፡ በምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና በግብርና ቢሮ ድጋፍ የሞላሰስና የዩሪያ ብሎክ የተባለ (MUB) መኖ በጓሮዋ ለማዘጋጀት ሞክራ ነበር፡፡ ሆኖም ሞላሰሱም ዩሪያም በአካባቢዋ በቀላሉ የሚገኙ ባለመሆናቸው መጠቀሙዋን አቋርጣለች፡፡ ስለዚህም አንድን ቴክኖሎጂ በቀላሉ ለመቀበል ግብአቶቹ በአካባቢው የሚገኙ ነገሮች መሆን አለባቸው የሚል አስተያየት ትሰጣለች፡፡

አርሶ አደር ጎረቤቶቿ እየወጣ ባለው የመኖ ዋጋ ውድነት እንዴት ከብቶቿን እንደዚህ በጥሩ ሁኔታ መመገብ እንደቻለች ይገረማሉ፡፡ እሷ ግን ሁሌም ትነግራቸዋለች፡፡ ከብቶች በአግባቡ ከተንከባከቧቸው፣ በጥሩ ሁኔታ ከበሉ፣ ንፅህናቸው ከተጠበቀ፣ በጊዜው ከታከሙ ለራሳቸው የሚሆን መኖ መግዣ ብቻ ሳይሆን በቂ ትርፍም እንደሚያስገኙ ታስገነዝባለች፡፡

## አነስተኛ ሀብት የሚጠይቁ ቴክኖሎጂዎችና የገበያ ምርቶችን ማስተዋወቅ

ሴቶች በዋና ዋና የግብርና ምርቶች ማምረቻ ግብአቶችና መሳሪያዎች ማለት መሬትና የእርሻ መሳሪያ የመሳሰሉት ላይ የማዘዝና የመቆጣጠር ወይም የማግኘት ሁኔታ በጣም አናሳ ወይም ጨርሶ የለም ማለት ይቻላል፡፡ በአብዛኛው የሚያስተዳድሩትና እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ወይም ምን ሊመረትበት እንደሚገባ የሚወስኑት ባሎቻቸው ናቸው፡፡ ለሽያጭ ወይም ለገበያ የሚቀርቡ ሰብሎችንና ጥራጥሬዎችን ለማምረት ሰፋፊ መሬት ያስፈልጋል፡፡ በአባወራ በሚመራ ቤተሰብ ውስጥ በነዚህ ሥራዎች ላይ ሴቶችን ማሳተፍ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁንና በእማወራ በሚመራ ቤተሰብና በመሬት ይዞታቸው የተሻለ የመቆጣጠር ዕድል ባላቸው ቤተሰቦች ውስጥ ሴቶችን ማሳተፍ ይቻላል፡፡

በግብርና ምርትና ገበያ ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ሰፋፊ መሬት በማይፈልጉ የምርት ዓይነቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በጓሮ ውስጥ የሚሰሩ የፍራፍሬ ዛፍ ችግኞችን ማፍላት ሰፊ መሬትና ብዙ ግብአት የማይጠይቁ ስለሆነ የመነሻ ካፒታል እጥረታቸው ከተቃለላቸው ለሴቶች ተስማሚ የሥራ ዘርፍ ነው፡፡

ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በመክተብ ዘዴ የተሻሻሉ የፍራፍሬ ዛፍ ችግኞችን የማምረት ሥራ ሴቶችን ዒላማ ባደረገ መልኩ በጎማ፣ በዳሌና በቡሬ ወረዳ የማስተዋወቅ ሥራ ሰርቷል፡፡ የማዳቀል ቴክኒክ በአካባቢው የፍራፍሬ አመራረት ላይ ማነቆ የሆነውን አሠራር ለማስቀረት የታለመ ነበር፡፡ ለምሳሌ የጎማ የሙከራ ወረዳ ማህበረሰቡ የሚያመርታቸው የተለያዩ የፍራፍሬ ዝርያዎች ስለ አመጣጣቸው ሆነ ስል አያያዛቸው ምንም አይነት መረጃ የሌላቸው ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ ፍሬ ለመስጠት ረጅም ጊዜ ወይም ለአሠራር የሚያመች ቁመት ያላቸው ከመሆኑም በላይ የሚያጠቃቸውን የበሽታና የተባይ ዓይነት ለማወቅ አዳጋች ሆኖአል፡፡

**የፍራፍሬ ችግኞችን ማምረት**

በጎማ ወረዳ ስድስት ሞዴል አርሶ አደሮች ( ሶስት ሴቶችና 3 ወንዶች ) አቦካዶ በመክተብ ስልጠና ተሰጥቷቸው 2052 የአቮካዶ ችግኝ በአለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁት ከሐስ፣ ኤቲንጀርና ፎርቴ (Hass, Ettinger, Fuerte) ከተባሉ ዝርያዎች ጋር በመከተብ አዳቅለው በ28 ገበሬ ማህበራት ውስጥ ለሚገኙ 763 ቤተሰቦች አንዱን ችግኝ በ25 ብር ሂሳብ ሸጡ፡፡ ገበሬዎቹ በጥቅሉ 42.000.00 ብር አግኝተዋል፡፡ ሶስቱ ሴት አርሶ አደሮች የችግኝ ማፍላቱ ሥራ ላይ ሲካፈሉ ሁሉንም ሥራ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየሰሩ ነው፡፡ አንደኛዋ ከቤት ሥራዋ በተጨማሪ የእርሻ ሥራ ልምድ ያላት ሲሆን ሁለቱ ግን የእርሻ ሥራ ልምድ አልነበራቸውም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሴቶች አንዴ የፍራፍሬ ዛፍ ችግኝ ማፍላቱ ሥራ ላይ ተሰማርተው ጥቅሙን ካዩ በኋላ በቀጥታ በእርሻ ሥራ ላይ ከነቤተሰቦቻቸው በመሳተፍ አፈር ማምጣት፣ የችግኝ ላስቲኮችን መሙላትና የፀሃይ መከላከያ ዳስ መስራት ላይ አተኮሩ፡፡ ምንም እንኳን ተጨማሪ የሥራ ጊዜ ቢኖረውም ሁሉም ሴት አርሶ አደሮች በዝግጅቱ የረኩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

**ከዲጃ ያሲን የፍራፍሬ ችግኝ አምራች**



ከጎማ ወረዳ የተገኘችው ከዲጃ ያሲን የ36 ዓመት ሴትና የ6 ልጆች እናት ናት፡፡ ባለቤቷ በወር 350 ብር የሚያገኝ የሂሳብ ሠራተኛ ነበር ሆኖም በ1998 ከስራ ተሰናብቷል፡፡ ተጨማሪ ገቢ ለቤተሰቧ የሚያስገኝ ሥራ በመፈለግ ላይ እያለች ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክትና የወረዳ ግብርና የፍራፍሬ ዛፍ ችግኝ ማምረትን በተመለከተ ያነጋግሯታል፡፡

> ያገኘሁት ዕውቀትና ሙያ እኔና ቤተሰቤ በቂ ገንዘብ አግኝተን ኑሯችንን ማሻሻል እንደምንችል በራስ መተማመንን አጎናጽፎኛል። ባለቤቴ ሥራ የፈታ ጊዜ ኑሯችን ምን ይመስል እንደነበር ማንም የመንደሩ ፍሪ ያውቃል፡፡ ለዚህም ነው ወንዱም ሆነ ሴቱ አርሶ አደር ለስኬት ትኩረት የሰጡት፡፡

ከሌሎች አርሶ አደሮች ጋር በመልካሳ የግብርና ምርምር ባለሙያዎች የአምስት ቀን በመክተብ የማዳቀል ስልጠና ትወስዳለች፡፡ ወዲያዉኑ ከስልጠናው በኋላ በስልጠናው ያገኘችውን ዕውቀት በመጠቀም ወደ ችግኝ ማምረቱ ሥራ ገባችና መትከል ጀመረች፡፡ በሚቀጥለው ዓመት 300 የአቡካዶ ችግኞችን ከመልካሳ ባገኘችው ቁርጥራጮች ከትባ ነበር ፡፡ ነገር ግን ግማሹ ብቻ ፀደቀላት፡፡

በከዲጃ እምነት ከመልካሳ ያገኘቻቸው ቁርጥራጮች በመንገድ ላይ እርጥበታቸውን ስላጡ ሳይፀድቁ መቅረታቸውን ገልጻለች፡፡ አሁን ደግሞ ከአራቱም ዝርያዎች አንዳንድ እናት ዛፍ (ከሐስ፣ ከፍሩቴ፣ ከኤቲንጀርና ከባከን ዓይነቶች) በምትኩ በመውሰድ ችግሩ እንደማይደገም እርግጠኛ ሆናለች፡፡ ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ ከያንዳንዱ ዛፍ 10 ኪሎ ግራም አቦካዶ አግኝታ ለቤት ፍጆታ አውላዋለች፡፡ በ2002 ዓም 300 የሚሆኑ የተሻሻሉ የአቦካዶ ችግኞችን በ25 ብር ሂሳብ በመሸጥ ወደ 7500 ብር ገቢ አግኝታለች፡፡ በ600 ብር ወይፈን ገዛች፡፡ አሁን የልጆቿን የትምህርት ቤት ክፍያና ልብስ እንዲሁም የቤት ወጪዋን ትሸፍናለች፡፡

## ኃላፊነቱን እንጂ ጥቅሙን በማይጋሩት የገበያ ምርቶች ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ

የምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) የሥርዓተ ፆታ ትንተና እንደሚያመለክተው ሴቶች በበግና ፍየል እርባታ ሥራ ውስጥ የጎላ ድርሻ ያላቸው ቢሆንም በአሻሻጥ ላይ ብዙም እንደማይሳተፉና ገቢውንም እንደማይቆጣጠሩ ይታወቃል፡፡ ከዚህም የተነሳ ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት አስፈላጊውን ስልጠና ለመስጠትና ብድርም በማመቻቸት የግብአትና የገበያ ተደራሽነታቸውን በመጨመር የሚያገኙትንም ገቢ መቆጣጠር እንዲችሉ ለማድረግ በሴቶች ላይ ያነጣጠረ ሥራ ለመስራት አቀደ፡፡

## በግና ፍየልን ማድለብ

በመኤሶ ሴቶች ከባሎቻቸው ጋር በመሆን በጎችና ፍየሎችን ያረባሉ፣ ይቀልባሉ፣ በየእለቱ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋሉ፣ በጠጣቸውን ይጠርጋሉ፣ ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው አካባቢ ከመሸጥና ከሽያጩ የሚገኘውን ገቢ ከመቆጣጠር የተገለሉ ናቸው፡፡ ሴቶች ከባሎቻቸው ጋር መክረውና ሸጠው ገቢውንም በጋራ የሚቆጣጠሩት በጣም በጥቂት ቦታ ነው፡፡ ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ሴቶችን ከፍየል እርባታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል መንገድ በማመቻቸት 189 ሴቶችን በሶስት ቡድን ከፍሎ መስራት ጀመረ፡፡ ፕሮጀክቱ በኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ማህበራት በኩል የ450 ብር ብድር ከሁለት እስከ አራት ፍየሎችን እንዲገዙና በዓመት በሶስት ዙር እንዲያደልቡ ብድራቸውንም በአንድ ዓመት እንዲከፍሉ አደረገ፡፡ በተጨማሪም የሙያ ማሻሻያ የቁጠባና የፍየል ማድለብ ሥራ ሥልጠና ተሰጣቸው ፡፡ ፍየሎቻቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲደልቡ ለማድረግ አረንጓዴ አልሚ ምግቦችን ለምሳሌ እንደ የስንዴ ገለባ፣ የበሰለ በቆሎና ዘንጋዳ የመሳሰለውን ያበላሉ፡፡



ከዲጃ ያዩ ፣ ሰዓዳ ሁሶ፣ አሊያ መሐመድ፣ መካ ሁሶ፣ ዛህራ አቡለሚት እና ደሀብ የተባሉት መኢሶ ‹‹ የሐዊ ጉዲና›› ቡድን አባላት ሲሆኑ በምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በኩል ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ማህበር እያንዳንዳቸው በ2001 ዓ.ም ለፍየል ማድለብ ስራ 450 ብር ብድር እንዲያገኙ ተደረገ፡፡ የተሰጣቸውን ስልጠናና የገንዘብ ብድር በመጠቀም እያንዳንዳቸው ከ6 እስከ 8 የሚደርሱ ፍየሎችን በሁለት ዙር በማድለብ በመጀመሪያው ስድስት ወር ከ1000 ብር እስከ 1600 ብር ለየራሳቸው ለማትረፍ ችለዋል፡፡ እነዚህ ሴቶች ስልጠና በመውሰዳቸው፡ ብድር በማግኘታቸውና በቡድን በመደራጀታቸው ራሳቸውን የቻሉ ፍየል አድላቢዎች ከመሆናቸውም በላይ በፍየል ግዢና ሽያጭ ሆነ ስለገቢያቸው አጠቃቀም ወሳኞቹ ራሳቸው ነበሩ፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው መነሻቸው የነበረውን 450 ብር ወደ 2500 ና ወደ 4000 ብር አሳድገው ብድራቸውንም በጊዜው ለመክፈል ችለዋል፡፡

## በወንዶች በሚዘወተሩ ተግባሮች ውስጥ ሴቶች የሚሳተፉበትን ዕድል ማፈላለግ

ብዙ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ልማዳዊና ተክለ ሰውነታዊ በሆኑ ምክንያቶች ሴቶች ከአንዳንድ የማምረትም ሆነ የግብይት ተግባራት እንዲገለሉ ተደርገዋል፡፡ ከብቶችን ማርባትና ንብ ማነብ ለዚህ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ ይህንን ክልከላ ሰብሮ ለመግባትና አጋጣሚውን በተገኘበት ጊዜ ለመጠቀም የክልከላውን ምክንያት በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

## ዘመናዊ ቀፎን ማስተዋወቅ ሁኔታዎችን ይለውጣል፡፡

በሀገራችን ልማድ መሰረት በብዙ አካባቢዎች ሴቶች የማር ምርት ከማምረትና ከመገበያየት የተገለሉ ናቸው፡፡ ለዚህ እንደዋና ምክንያት ሊወሰድ የሚችለው በባህላዊ የንብ ማነብ ዘዴ ቀፎዎች የሚሰቀሉት በረጃጅም ዛፎች ቅርንጫፍ ላይ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በተክለ ሰውነታቸው ምክንያት ዛፍ ላይ ለመውጣትና ቀፎዎችን ትክክለኛ ቦታቸው ላይ ለማሰር ወንዶች የተሻሉ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በተጨማሪ በባህላዊ የንብ ማነብ ዘዴ ቀፎዎች የሚሰቀሉት ጫካ ውስጥ ስለሆነ ሴቶች ብቻቸውን ጫካውን ለማቋረጥ ለደህንነታቸው ጥሩ ባለመሆኑ ነው፡፡

ነገር ግን በአዲስ ወይም በዘመናዊ የንብ ማነብ ዘዴ ባህላዊውም ሆነ ዘመናዊ ቀፎዎች በቤት አካባቢ በጥላ ሥር መሬት አጠገብ ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሴቶች በንብ ማነብ ወይም ማር ምርትና ገበያ ላይ አስፈላጊው ዕውቀትና ስልጠና ካላቸው በሥራው መሳተፍና የእለት ተዕለት ሥራቸውን ማከናወን ይችላሉ ማለት ነው፡፡

በፎገራ ወረዳ በንብ ማነብና ማር ምርት ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሻሻል ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ከአጋሮቹ ጋር በመሆን ሁለት ጊዜ ስልጠና አዘጋጅቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የጥንዶች ስልጠና አስፈላጊ ነበር፡፡ ምክንያቱም በቤተሰብ ደረጃ የሚደረጉ ውሳኔዎችን ለማሻሻል ጠቃሚ በመሆኑ ነው፡፡ በውጤቱም ከስልጠናው በኋላ የሴቶች ተሳትፎ ጨመረ፡፡ በመስክ ደረጃ በተደረገ የዳሰሳ ጥናትም እንደታየው ምንም እንኳን የልማድ ተፅእኖ ቢኖርም በመስክ ሰራተኞች ብርቱ ድጋፍ ደረጃ በደረጃ የሴቶች በንብ ማነብ ስራ መሰማራት እየጨመረ መሆኑን ያሳያል፡፡

ብዙ ንብ አናቢዎች እንደሚሉት አዲሱ የንብ ማነብ ዘዴ ከልማዳዊው ይልቅ የተሻለና ቀላል በመሆኑ በሴቶች ሊተገበር የሚችል ነው። ከላይ ዘርግ የሆነው አዲሱ ቀፎ በጥሩ ሁኔታ ለማሸግ፣ ለማጠን፣ የንብ መንጋውን ከጉንዳንና ከሸረሪት ለመጠበቅ፣ ውስጡን ለመቆጣጠር ፣ ወዘተ የተመቸ በመሆኑ በቀላሉ በሴቶች ሊሠራ ይችላል። ባሎቻቸው በማይኖሩበት ጊዜ እንኳ የጎረቤት ወንዶችን እርዳታ ሳይጠይቁ ማሩን በቀላሉ መቁረጥ ይችላሉ።

እስከ አሁን ድረስ ከአዲሱ ቀፎ የሚመረተው ማር የገበያ ትስስሩ በጣም ደካማ ነው። የዋጋ ውጣ ውረድም አለበት። ስለዚህ ለማር የተሻለ የገበያ ትስስር መፍጠር አስፈላጊ ነው።



## ሴቶች የዳልጋ ከብቶችን እንዲያረቡ ማበረታታት

በሁሉም ፕሮጀክቱ በሰራባቸው ጣቢያዎች ከብቶች የሚረቡት ለሽያጭ ሲሆን ስራውም በወንዶች የበላይነት የተያዘ ነው። ምንም እንኳን በአንዳንድ ጣቢያዎች አንዳንድ ሥራዎች ወንዱና ሴቱ ተጋግዘው የሚሰሩት ቢሆንም ለምሳሌ በመተማና በፎገራ ድርቆሽ ማዘጋጀት፣ በመዔሶ ተጨማሪ ምግብ ማምጣት፣ በአድአ ማዳቀል፣ ቀለብና የየቀኑን ሥራ መከታተል ቢኖርም የደለቡትን ከብቶች የሚሸጡትና ከሽያጩ የተገኘውን ገቢም የሚቆጣጠሩት ወንዶች ናቸው።

በመተማ ምርታማነትና የገበያ ስኬት ፕሮጀክት ብድርና የአስሮ መቀለብ ዘዴ ባስተዋወቀበት አካባቢ ለተወሰኑ የወንዶችና የሴቶች ቡድን የዳልጋ ከብቶች ማድለብ ዘዴ ስልጠና ተሰጠ።

አብዛኛዎቹ የሴቶች ቡድን አባላት ባል የሌላቸው እንደመሆናቸውና የሚቀለቡት ከብቶች በቤት አካባቢ በመሆናቸው አስሮ መቀለብን የወደዱት ይመስላል፡ ፡ ከሦስት ወራት የማድለብ ሥራ በኋላ ከብቶቹ ሰውነት ስለሚደርቡና ክብደት ስለሚጨምሩ የተሻለ ዋጋ ያወጣሉ። ምንም እንኳን የአርሶ አደሩና የነጋዴው ግንኙነት የሰመረና የገበያ ዕድሉ የሰፋ ቢመስልም የተለያዩ ተግዳሮቶች ማጋጠማቸው አልቀረም። የሙያ ትምህርት ማነስ፣ የከብቶች በሽታ፣ የከብት ማቆያ በረቶች ችግር፣ በበጋ ወራት የመኖ እጥረት (ሰፊ የግጦሽ መሬት ቢኖርም) ደካማ የውጪ ላኪዎች ግብይትና ሥራውን ለመደገፍ አነስተኛ የብድር መጠን መኖር የመሳሰሉት ችግሮች ተስተውለዋል።

**እልፍነሽ፣ -- በአድአ ወረዳ ሞዴል ንብ አናቢ**

በለጋ እድሜዋ የተዳረችው እልፍነሽ በርመጂ ከአድአ ወረዳ በአካባቢው ለሚገኙ ባለርስቶች ንብ አናቢ ሆኖ ከሚሰራው አማቿ የንብ ማነብ ሥራን ተማረች። የአካባቢው የልማት ሠራተኞች ሲያገኟት ስለ ዘመናዊ የሽግግር ቀፎ፣ ስለንብ መኖ፣ እንዲሁም ስለተጨማሪ መኖዎች ሁኔታ ስልጠና ወሰደች።

በተጨማሪ የንብ ቀፎዎችን እንዴት በንፅህና መያዝ እንደሚገባ፣ ውሃ ባካባቢው በማኖር እንዴት ንቦች አካባቢያቸውን እንዳይለቁ ማድረግ እንደሚቻል ተረዳች።

ብድርም እንድታገኝ ተደርጎ ዕዳዋንም በጊዜው ለመክፈል ችላለች። ከንብ ማነቡ በተጨማሪ ወ/ሮ እልፍነሽ የእርሻ ሥራም ትሰራለች። በያዘችው 4 ሄክታር መሬት ላይ 3 ጨምራ በመከራየት ባቄላ፣ ጤፍ፣ ስንዴና አተር ታመርታለች። ከዚህም በተጨማሪ 2 ላሞች፣ 6 በጎች፣ 2 ዶሮዎችና 4 አህዮች አሏት።

በ3 ባህላዊ ቀፎዎች ጀምራ ዛሬ 9 የሽግግር 3 ዘመናዊና 4 ባህላዊ ቀፎዎች አሏት። በዓመት ሁለት ጊዜ ማር ታመርታለች። ባለፈው ዓመት 210 ኪ.ግራም ማር አምርታ ኪሎውን በ40 ብር ሂሳብ ሸጣለች። ንብ ማነብ በጣም ቀላል ነው ትላለች፣ ንፅህናቸውን መጠበቅ፣ በበጋ ወራት ተጨማሪ ምግቦችን ማዘጋጀትና ባካባቢው ተክሎች እንዲበቅሉ ማድረግና ንቦች ምግብና ውሃ ፍለጋ ሩቅ መንገድ ሄደው በዚያው እንዳይጠፉ ማድረግ ነው።

ወ/ሮ እልፍነሽ ዘመናዊ የንብ ማነብ ሥራዋን የማስፋፋት ዕቅድ አላት። ምክንያቱም በእርጅና ዘመኗ ይህን ሥራ መስራት ስለምትፈልግ ነው። በአካባቢዋ ሞዴል አርሶ አደርና ብዙ ማምረቻ መሳሪያዎችን የተሸለመች ሴትም ናት።

**በመተማ በቤት አካባቢ ከብቶችን ማርባት**

ወ/ሮ እናንዬ በሞት ከተለዩዋቸው ባለቤታቸው የወረሱዋቸውን ከብቶች በማድለብ ሥራ ተሰማሩ። የ35 ዓመት ዕድሜ የነበራችውና የ4 ልጆች እናት የሆኑትን እናንዬን በቅድሚያ ለከብት ማድለቡ ሥራ ያዘጋጇቸው የወረዳው የግብርናና የገጠር ልማት ሰራተኞች ናቸው።

ሥራውን ሲጀምሩ ሁለት በሬዎችን ይዘው የተሳካ የማድለብ ሥራ አከናውነዋል። ምክንያቱም እሳቸውና ሌሎች አርሶ አደሮች የገበያ ትስስራቸው መልካም ስለነበረ ነው። ያደለቡዋቸውን ከብቶች በ3000 ብር ትርፍ ሸጠዋል። ስራውን ለመቀጠል ሁለት በሬዎች በድጋሚ ገዝተዋል። በዚህ ዙር ግን የገበያው ዋጋ ዝቅ ያለና የገበያ ትስስሩም ደካማ ስለነበረ በራሳቸው መንገድ ሄደው የደለቡ በሬዎችን ሸጡ። ነገር ግን የተገኘው ትርፍ አናሳ ነበር። ከሥራው ያገኙት ገቢ ግን በጎንደር ቤት ለመግዛት አስችሏቸዋል። የከብቶቹንም ቁጥር አሳድገው አሁን 4 ላሞች፣ 6 በሬዎችና ጥቂት ፍየሎች አሏቸው። እናንዬ ወተት በመናጥ በየ 4 ወሩ 42 ኪሎ ግራም ቅቤ ይሸጣሉ።

ውጤታማ መሆናቸውን ከተመለከቱ በኋላ ብዙ ሴቶች ፈለጋቸውን ተከተሉ። ለስኬታቸው ምክንያት የሆናቸው ‹‹ተስፋና ተነሳሽነቱ›› እንደሆነ ይናገራሉ። የመጀመሪያው ባለቤታቸው ሲሞቱ ለልጆቻቸው እሳቸው ብቻ እንዳሉዋቸውና በቤቱም በርሻውም ኃላፊነቱን በሙሉ መሸከም እንዳለባቸው ተገንዝበው ነበር። አሁን ግን ተጨማሪ መሬት አግኝተው ከአዲሱ ባለቤታቸው ጋር የውሃ ፓምፕ ገዝተው የጓሮ አትክልት በማልማት ላይ ተሰማርተዋል።

**እንደኔ ያሉ አርሶ አደሮች ሁሉ የተደረገልንን የገበያ ትስስር ድጋፍ በጣም እናደንቃለን፡፡ ድጋፉን ወደፊትም እንፈልገዋለን፡፡**



## ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ሰብሎች እንዲያመርቱ ሴቶችን ማበረታታት

ምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በሚንቀሳቀስባቸው ወረዳዎች በሙሉ በአትክልት ምርት ሂደት ውስጥም እንደ ሌሎቹ የማምረቻ መሳሪያዎች ሁሉ መሬት፣ የመስኖ ውሃና ውሃ ማጠጫ መሳሪያዎች በወንዶች በሚመሩ ቤተሰቦች ቁጥጥር ስር ያሉ ናቸው፡፡ አነስተኛ መሬት ያላቸው በእማወራ የሚመሩ ቤተሰቦች ሁሌም አትክልት ከማልማት ይልቅ ለምግብነት የሚውለውን የጥራጥሬ እህል ወደ ማምረት ያዘነብላሉ፡፡ አብዛኛው በእማወራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ምርታቸውን ለበሬና ለጉልበት ኪራይ ያካፍላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ምን መመረት እንዳለበት የሚወስነው ተካፋዩ ወገን በመሆኑ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን እንደ አትክልት ምርት የመሳሰሉትን ግን ደግሞ ከፍተኛ ጉልበትና ጊዜ የሚጠይቁትን፣ በተለይ መሬትን ለመስኖ ማዘጋጀትና የመሳሰሉ ሥራዎች ያሉበትን ተግባር ለማከናወን ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡



## በተፈጠረው ሁኔታ በመጠቀም እድገቱን ማስቀጠል ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ ተቋምነት መሸጋገር፡፡

የምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት ሴቶች በስፋት የሚካፈሉበትን መስክ ለምሳሌ ዶሮ እርባታ፣ የወተት ምርትና በግና ፍየል ማርባት ላይ መሻሻል እንዲመጣ ከተፈለገ ቀላሉ ዘዴ ሴቶችን ኢላማ አድርጎ መነሳት እንደሆነ ተገንዝቧል፡፡ ሴቶች በራስ መተማመን ሊኖራችው የሚችለው የማምረቱና የግብይቱን ሂደት በተመለከተ ልምዱና ክህሎቱ ባላቸው ሙያ ሲሰማሩ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ሌላው ፕሮጀክቱ የተገነዘበው ነገር ቢኖር ሴቶች በሥራ አመራር ችሎታቸው እንዲሻሻሉ ከተደረገ በወንዶች የሚሰራው ሥራ ላይ የመሳተፍ ፍላጎት እያደረባቸው እንደሚሄድና የተቋማቸውን ሥራ ሰፋ በማድረግ አዳዲስና ከፍ ያለ ዋጋ ባላቸው ሥራዎች ላይ የመሳተፍ አዝማሚያ እንደሚያሳዩ ነው፡፡ ለምሳሌ በዳሌ ወረዳ የመጀመሪያ ምርታቸው የሆነውን የቄብ ዶሮዎች ሽያጭ እንዳከናወኑ ወዲያውኑ ወደ በግ ማድለብ ሥራ የገቡ ሴቶች አሉ፡፡ በጎማ ወረዳ ደግሞ አንዳንድ ሴቶች የፍራፍሬ ችግኝ ከሸጡ በኋላ ባገኙት ገንዘብ ወይፈን ገዝተዋል፡፡ በመኢሶ ደግሞ በፍየል ማድለብ ስራ ከተሰማሩት ሴቶች ግማሾቹ ወደ ከብት ንግድ ተሸጋግረዋል፡፡

ይህንን ሽግግር ተከትሎ የሚፈልጉትን ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻል ፕሮጀክቱ 450.00 ብር የነበረውን የብድር መጠን ወደ 1200.00 ብር ከፍ አድርጓል፡፡

### ወ/ሮ አሰሉ በአላማጣ ሽንኩርት ሻጭ

ወ/ሮ አሰሉ የአንድ ሴት ልጅ እናት ናት፡፡ ዕድሜዋ 35 ዓመት ሲሆን የምትኖረውም በአላማጣ ወረዳ ነው፡፡ የጥራጥሬ እህሎችን እንደበቆሎ፣ ጤፍ የመሳሰሉትን ብቻ ባላት አንድ ሄክታር መሬት ላይ በማምረት ነበር ኑሮዋን የምትገፋው፡፡ በወንዝ ዳርቻ ሽንኩርት የሚያመርቱ ወንዶች ገበሬዎችን ካየች በኋላ ከዘመድ የተሰጣትን ለመስኖ የሚሆን መሬት ተጠቅማ ሽንኩርት ለማምረት ወሰነች፡፡ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበር አባልም ሆነች፡፡ በምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት አማካኝነት ስለ ሽንኩርት አመራረትና መስኖ አሰራር ባገኘችው ዕውቀትና ሙያ ተጠቅማ የሽንኩርት ምርቷን ለማሳደግ ችላለች፡፡

አንድ ጊዜ ወ/ሮ አሰሉ ከሕብረት ሥራ ማሕበራቱ ጋር በሽንኩርት ዋጋ ላይ እየተነጋገረችና ከጓደኞቿ ጋር ምርቷን ለመሸጥ እየተዘጋጀች እያለ አንድ ችግር ገጠማት፡፡ ከመቀሌ የመጡ የሽንኩርት ደላሎች ሁሉንም የሽንኩርት ምርት በርካሽ ዋጋ ገዝተው ለማትረፍ ፈለጉ፡፡ ነገር ግን አሰሉ አስቀድማ ዋጋውን ታውቅ ስለነበር ለማረጋገጥ ወደ መቀሌ ደውላ ደላሎቹ ያቀረቡት ዋጋ ትክክል እንዳልሆነ አረጋገጠች፡፡ ዋጋው ሰዎቹ እንዳቀረቡት በኩንታል 100 ብር ሳይሆን በኩንታል 160 ብር እንደሆነ ተነገራት፡፡ ይህንኑ ከባልደረቦቿ ጋር ተነጋገረችና ሽንኩርቱን ለደላሎቹ ላለመሸጥ ወሰኑ፡፡ በዚሁ መሀል ከሌሎች የግዢ ምንጮች ጋር ተደዋውላ ደላሎች ሳያውቁ ከሌላ ገዢ ጋር ተዋዋለች፡፡ ሆኖም ገዢዎቹ መጫኛ መኪኖቻቸውን ይዘው መጥተው ሊጭኑ ሲፈልጉ ደላሎቹና የአካባቢው ነጋዴዎች ስለተቃወሙዋቸው ሳይጭኑ ተመለሱ፡፡ የአካባቢው ነጋዴዎችና ደላሎች ለነሱ እንድትሸጥላቸው ለማድረግ ብዙ ጣሩ፡፡ ነገር ግን አሰሉ በእምቢተኝነቷ ፀንታ አላማጣ ሄዳ መኪና ተከራይታ በማምጣት የራሷን ሽንኩርት ጭና በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ በቅታለች፡፡

በአንድ ጊዜ ምርት ብቻ ብዙ በማትረፏ በገርጀሌ ከተማ በ8000.00 ብር ቤት ለመግዛት ችላለች፡፡ የቤት እቃዋንም አልጋና ፍራሽ ጨምሮ አሟልታለች፡፡ የቤቷንም ወጪ የመሸፈን ሀላፊነቷንም በሚገባ ተወጥታለች፡፡

**የአሊያ መሓመድ ወደ ከብት ንግድ መግባት**

አሊያ መሃመድ በመዔሶ የምትኖር የ6 ልጆች እናት የሆነች የ47 ዓመት ሴት ናት፡፡ እንደ ምርታማነት እና ገበያ ስኬት ፕሮጀክት የለውጥ ውጥን አካል የ450.00 ብር ብድር፣ በፍየል ማድለብ ሙያ ላይ በፕሮጀክቱና በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሠራተኞች ትብብር የተዘጋጀውን የ7 ቀን የአሰራር ማሻሸያና የቴክኒክ ስልጠና ወሰደች፡፡ በወሰደችው የብድር ገንዘብ ሁለት ፍየሎችን በ430 ብር ከቤካ ገበያ ገዛች፡፡ ተባዮቹን ከላያቸው አፅድታ በቆሎ ዱቄት የተጠበሰ ዘንጋዳና አገዳውን ለ3 ወራት አበላች፡፡ ከሦስት ወራት በኂላ በ800 ብር ሸጠቻቸው፡፡ አሁንም አራት ፍየሎችን በ900.00 ብረ ገዝታ ለሦስት ወር ቀለበቻቸው፡፡ አራቱንም በ1600 ብር ሸጠቻቸው፡፡ በሦስተኛው ዙር በገበያ ውስጥ ያለውን ፍላጎት በመመልከቷ ወደ ከብት ንግድ ለመሸጋገር ወሰነች፡፡ ከዚህም ሌላ የምትገዛቸው ፍየሎችም ዋጋቸው እየጨመረ ስለመጣ ትርፏን ሊያሳንሰው እንደሚችል በማወቁዋ ወደ ሌላ መሸጋገሩ አስፈላጊ መሆኑን ወሰነች፡፡ በሚቀጥለው የገበያ ቀን አንድ በሬ በ1200 ብር በመሸጥ በአንድ ሳምንት ሶስት መቶ ብር ለማትረፍ ችላለች፡፡ በዚህ ዘዴ በተደጋጋሚ ተጠቀመች፡፡ በሁለት ወራት ውስጥ አራት ጊዜ ከብቶች ገዝታ በመሸጥ ከ200-250 ብር በያንዳንዱ ሽያጭ እያተረፈች በዘጠኝ ሳምንት ውስጥ 1100.00 ብር ንፁህ ትርፍ አገኘች፡፡ ባገኘችው ውጤት ተገፋፍታ አንድ በሬ በ3500.00 ብር ገዝታ ለአንድ ወር ቀልባና አድልባ በ4500 ብር ሸጠች፡፡ በዚህ መልኩ እየሰራች የወሰደችውን ብድር በጊዜው በመጨረሷ ሌላ የ1200 ብር ብድር ሥራዋን ለማሻሻል እንዲረዳት ብላ ወሰደች፡፡ ባላት ገንዘብ ላይ ጨምራ በ6000 ብር አንድ በሬ ገዝታ ሦስት ወር አደልባ ከ8000.00 እስከ 9000.00 ብር ለመሸጥ አቅዳለች፡፡



## ማጠቃለያ

ሴቶች ሰፊውን ድርሻ የሚወስዱበት ማንኛውም የልማት ሥራ የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታን በማሻሻል፣ የምግብ ዋስትና እጦትን በመዋጋትና ድህነትን በመቅረፍ ረገድ ስኬታማ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

ሴቶች ለኢትዮጵያ ገጠር ልማት አንቀሳቃሽ ሆነው እያለ ከድካማቸው የሚያገኙት ጥቅም ግን የተመጣጠነ አይደለም፡፡ በተለይ በግብርና ምርቶች ግብይት ውስጥ ፍትሀዊ ያልሆነ የጥቅም መጋራት ይስተዋላል፡፡

ለዚህም ምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት (IPMS) በውል የታሰበ ስልት ነድፎ አብዛኛው በፕሮጀክቱ የታቀፉ ሴቶች ከእሴት ሰንሰለቱ የተሻለ ጥቅም እንዲያገኙ ጥረት አድርጓል፡፡ ፕሮጀክቱ በአንዱ ወረዳ ጥሩ ስኬት ሲኖረው በሌላው ደግሞ አነስተኛ ስኬት ያስመዘገበበት ሁኔታ አለ፡፡

ነገር ግን በፕሮጀክቱ አስፈጻሚዎች አስተሳሰብ ከፕሮጀክቱ የተገኙ 10 የአፈጻጸም ተሞክሮዎች ለገጠሪቱ ኢትዮጵያ ግብርና ልማት ይጠቅማሉ ብለው ያምናሉ፡፡

## በኢትዮጵያ ግብርና ውስጥ የሴቶችን የልማት ውጤት ለማጠናከር የሚጠቅሙ አሥር ነጥቦች

### 1 የአስተሳሰብ ለውጥ

በማንኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ ወንድ ሆነ ሴት ኂላ ቀር የሆነውን ልማዳዊ አስተሳሰብና አሰራር በመተው በኢትዮጵያ ገጠር ልማት ውስጥ ሴቶች ያላቸውን አቅምና ፍላጎት በመረዳት በሰፊው እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 2 ማበረታቻ መስጠት

ሴቶች በስልጠናና በክህሎት ማሻሻያ መርሀ ግብሮች ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት የልማት ሠራተኞች የአፈጻጸም ምዘና አንዱ ነጥብ ሊሆን ይገባል፡፡

### 3 የሥርዓተ ፆታ ግቦችን ከፍ ያለ ግን ሊደረስበት የሚችልና ተጨባጭ አድርጎ ማቀድ

የልማት ፕሮጀክቶች መጀመሪያ ላይ ሲታቀዱ በልማቱ መሳተፍ የሚገባቸውን የሴቶች ቁጥር ከፍ አድርጎ ነገር ግን ተጨባጭ በሆነ መልኩ ሊተገበር የሚችል መሆኑን ተገንዝቦ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

### 4 ከወንዶችም ከሴቶችም ጋር አብሮ መስራት

በሁሉም የሥርዓተ ፆታ የልማት ሥራዎች ውስጥ አባወራውና ባለቤቱ አብረው እንዲካፈሉ ማድረግ ወንዱም ሴቱም አብረው በመሳተፍ የቤተሰብ ገቢያቸውን የማሳደግ ጉደይ ላይ እንዲረዳዱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ አሠራር በሌላ ጎኑ ደግሞ የሴቶችን ውሳኔ የመስጠት አቅም እያጎለበተ ይሄዳል፡፡

## 5 በሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ላይ ጥበብ የታከለበትና ተስማሚ አካሄድ መምረጥ

ሴቶችን ዓላማ አድርገው የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ቀድሞውንም በሴቶች ይሠሩ በነበሩእንደወተትምርት፣ አነስተኛእንስሳት እርባታ፣ የዶሮ እርባታ፣ ንብ ማነብና የጓሮ አትክልት ልማት ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በመነሳት ገበያቸው እየጨመረ ሲሄድና አቅማቸው ሲጎለብት የተሻለ ትርፍ ሊያመጣ ወደሚችል ከፍ ያለ ከብቶችን ማድለብ በመሳሰለ ሥራ ሊሰማሩ ይችላሉ።

## 6 ስልጠናዎችን ለሴቶች እንደሚስማሙ አድርጎ መንደፍ

የሴቶችን የግብይት ተሳትፎ ለማስፋት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ሲዘጋጁ ሴቶች በአብዛኛው የጊዜ እጥረት፣ በራስ የመተማመን ችግር፣ የክህሎትና የመተባበሪያ መንገድ ማግኛ ሁኔታዎች ውሱንነት እንዳለባቸው ማሰብ ያስፈልጋል።

## 7 የግብዓትና ያገልግሎቶችን አሰጣጥ በእሴት ሰንሰለቱ ፍሰት ውስጥ ማመቻቸት

መንግስት የግል ሴክተሩንና የገጠር የልማት ኢንተርፕሬነሮችን ግብዓትና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ማበረታታት አለበት።

## 8 ሴቶችን ከገበያ ጋር ማገናኘት

በገበያ መር የግብርና ልማት ውስጥ ወንዶችና ሴቶችን የሚያሳትፉ ዕድሎችን መፍጠር። ለምሳሌ አስፈላጊ ወደ ሆኑ ውይይቶች መጋበዝ፣ የሚሉትን ጆሮ ሰጥቶ ማዳመጥ፣ ፍላጎታቸውንና የልብ ፈቃዳቸውን በመረዳት ወደገበያ መግባት ለሚፈልጉ ሁሉ የግንኙነት መስኩና ለሴቶች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ።

## 9 ስለራሳቸው ያላቸውን አመለካከት መለወጥ

ሴቶች በግብርና ምርት የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ዋነኛ አገናኝ መሆናቸውን እንዲረዱ ማስቻል። በሌሎች የአለማችን ክፍሎች እንደሚደረገው ሁሉ የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴቶች ራሳቸውን እንደ እርሻ ሠራተኛ እና አገልጋይ እንጂ እንደ ቤተሰብ መሪና እንደ ገቢ አምጪ አያዩም። ይህንን አመለካከት ለመለወጥ ሴቶች ለተሻለ እና ጥራት ላለው መረጃ ቅርበት ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም ደግሞ የተሻለ የግንኙነት ትስስር ፈጥረው ሞዴል ኢንተርፕሬነር ሴቶችን ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## 10 ስኬቶች ከየአካባቢው የተለየ ሁኔታ ጋር ሊስማሙ በሚችሉበት ሁኔታ እንዲዛመቱ ማድረግ

የግብርና የውስጥ ድጋፍ መርሀ ግብሮች በአንድ ቦታ ላይ መልካም ውጤት ሲያስገኙ በሌላው ካባቢ ደግሞ ላያስገኙ ይችላሉ። ስለዚህ ምንግዜም ተሞክሮዎች ከአካባቢው ጋር እንዲዛመዱ ማድረግና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችም ለየአካባቢው ወይም ለአንድ የተለየ ቦታ ተስማሚ እንዲሆን አድርጎ ማቅረብን መርሳት የለብንም።

## ዋቤ ጽሁፎች


Belete A., Azage T., Fekadu B. and Berhanu G. 2010. Cattle milk and meat production and marketing systems and opportunities for market-orientation in Fogera woreda, Amhara region, Ethiopia. IPMS Working Paper 19. Nairobi, Kenya, ILRI.

Everts, S. 1999. Gender and technology. Empowering women, Engendering Development. Zed Books Ltd, London and New York

FAO, IFAD, ILO. 2010. Gender dimensions of agricultural and rural employment: Differentiated pathways out of poverty status, trends and gaps. Rome, Italy.

Torkelsson A, Tassew B. 2008. Quantifying women's and men's rural resource portfolios–empirical evidence from Western Shoa in Ethiopia. The European Journal of Development Research 20(3) 462—481

Kristjanson P., Waters-Bayer A., Johnson N., Tipilda A., Njuki J., Baltenweck I., Grace D. and MacMillan S. 2010. Livestock and women's livelihoods: A review of the recent evidence. Discussion Paper No. 20, Nairobi, Kenya, ILRI.

Aregu L., Bishop-Sambrook C., Puskur R. and Tesema E. 2010. Opportunities for promoting gender equality in rural Ethiopia through the commercialization of agriculture. IPMS Working Paper 18. Nairobi, Kenya, ILRI.

Mohamed A.M. Ahmed, Simeon E. and Assefa Y. 2004. Dairy development in Ethiopia. EPTD Discussion paper No. 123. IFPRI.

Quisumbing, A. R. and Pandolfelli, L. 2010. Promising approaches to address the needs of poor female farmers: Resources, constraints and interventions. World Development, Elsevier, vol. 38(4) 581-592.

World Bank 2008a. Ethiopia at a glance. World Bank. Washington, DC.

http://countrystudies.us/ethiopia



ይህ ሪፖርት በለምለም አረጉ፣ ራንጂታ ፑስካር፣ ጄኔቪየቭ ሬናርድና ደርክ ሆኬስትራ ከሱዛን ማክሚላን ጋር በመሆን ተዘጋጀ፣ በአፖሎ ሀብታሙ ተሰናድቶ በኢልሪ ታተመ፡፡ (ግንቦት 2003)

## ለህትመቶችና ሌሎች ዶክመንቴሽን




ፕሮጀክት ድረ ገፅ: http//:www.ipms-ethiopia.org

የኢትዮጵያ ግብርና ፖርታል: http//:www.eap.gov.et

CGIAR

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE

Canadian International Development Agency | Agence canadienne de développement international

በኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
Federal Democratic Repulic of Ethiopia Ministry of Agriculture


የህ ፅሁፍ ክርኤቲቭ ኮመንስ የሚባለውን የፈጠራ መብት የያዘ ስለሆነ ያለ ባለመብቱ ፍቃድ ከንግድ በስተቀር ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡ ታህሳስ 2005